የሞት መደንገጥ



ደሴ አዳም / 2014

“ሞትን በሙታን አትልመደው፤ ህያውነትን
በህያዋን አንድ!”

መግቢያ

መጽሐፉ በዓለም የሚኖር አብዛኛው የሰው ልጅ ጉንትም፣ዛሬም ሆነ ነገ ከሰጋ ሞት ለማምለጥ የማይፈነቅለው ደንጋይ፣ የማይወጣው ዳገት፣ የማይወርደው ቁልቁለት የማይሞክረው ሙከራ እንደሌለ... በሳይንሳዊ መንገድም ሆነ በባህሉ ይሄን ለማድረግ መጣሩን፣ ሆኖም ግን አንዱም በስኬት የተሞላ አለመሆኑን በመግለጽ ከተለያዩ ምንጮች እና መረጃዎች በመነሳት ሰዎች እንዴት ከሰጋ ሞት ማምለጥና እስከ ዓለም ፍጻሜ ሊኖር እንደሚችሉ ፍንጭ ለማሳየት ይሞክራል። ሁሉም ሰው ሞትን ይፈራል ከሞት የሚቀር ባይኖርም ከሞት አምልጦ እስከ ዓለም ፍጻሜ ለመኖር የሚያስችሉ መንገዶችን እያሳየ ለተሻለ ጥናት ይገፋፋል።

መልካም ንባብ!

አንድ

ወደ ሞት ጉዞ

ጠዋት ከእንቅልፌ ስነሳ መብራት በርቶ ነበር። ፊቴን እያባበስሁ ከአልጋዬ ተነሳሁ ፊቴን ታጥቤ ጸሎት ካደረግሁ በኋላ ሰዓቱ ደርሶ አባ ባህሪ ዘንድ ከመሄዴ በፊት አልጋዬ ላይ ተቀምጬ ሀሳቤን እና ቀልቤን የሳበውን መፅሐፍ ገልጬ ማንበብ ጀመርኩ።

ትናንት ማታ ስለ ሰሎሞን ዘመን ታሪክ የሚያወራው ገጽ ላይ ከመድረሴ በፊት ነበር መብራት የጠፋው። የጀመርሁትን ታሪክ እስከጨርስ ውስጤ ጓጓ። ማንበቤን ቀጠልኩ...

...ንጉስ ሰሎሞን ለልጁ ለንጉሥ ቀዳማዊ ምኒሊክ ወደ እርሱ በላካቸው መልዕክተኞች እጅ መልሶ እንዲህ የሚል ሀሳብ ያለበት መልዕክት ላከ።

"የሆነው ሁሉ የፈጣሪ ፍቃድ እንደሆነ፤ ሁሉም ቅርስ እና መጽሐፍትም ኢትዮጵያ ውስጥ እንዲቀመጡ ፍቃዱ ስለሆነ እንጅ ፈጣሪ ባይፈቅድ ቅዱስ ታቦታቱን ጨምሮ ንዋየ ቅዱሳቱ እንዲሁም ቅዱሳን መጽሐፍቱ ባላቸው ኃይል የእርሱ ቃላት እና ማወደሻ በመሆናቸው መጀመሪያም ከስራኤል እንደማይወጡ" ጻፈለት። ወደ ንጉሥ ሰሎሞን የተላኩት የእስራኤል እና የኢትዮጵያውያን መልዕክተኞችም ይሄን መልዕክትም ይዘው ወደ ኢትዮጵያ በሰላም ተመለሱ።

ዘመናት አለፉ ሰሎሞንንም አረጀ። ማረፊያውም ሲቃረብ ፈጣሪውን ከአስፈሪው ሞት እንዲሰውረው ከምድር በታች ትቢያ ሆኖ እስከ ዓለም ፍፃሜ እንዳይኖር ጠየቀ። አጥብቆም ተማፀነ።

የተሰጠው ጥበብ ባደረሰው ልክ አሱም እንደ ሄኖክ ላለመሞት
አጥብቆ ፈለገ። ያን የሚያደርግበት ኃይል ደግሞ በፈጣሪ በመልክ
ዼዴቅ ለማካኝነት የተጻፈ ለሄኖክ እንደተሰጠ እና ሄኖክም ያንን
ከሞት ማምለጫ ጥበብ በእግዚአብሔር አምነው ትዕዛዙን
ለሚፈጽሙ ጽፎ ለልጅ ልጆቹ እንዳስተላለፈ ተረዳ። የሄኖክን
ያለመሞት በህይወት የመኖርን ሚስጢር ደረሰበት። ነገር ግን ያ ሄኖክ
ለልጅ ልጆቹ ያስቀመጠው የህይወት መጽሐፍ በእጁ አልነበረም።
በአጠገቡ ያሉ የጭፍሮች አለቆችን ጠርቶ ከሞት የሚሰውር ጥበብ
ያለበትን የህይወት መጽሐፍን እንዲያመጡለት አዘዘ። የጭፍሮች
አለቆችም የታዘዙትን ፈጸሙ። በየቦታው የህይወትን መጽሐፍት
ለንጉሳቸው አፈላለጉ። መጽሐፉን ግን ሊያገኙት አልቻሉም።
ለንጉስም በእልፍኙ ገብተው አለማግኘታቸውን ነገሩት። ንጉስ
ሰሎሞን ግን በህይወት ለመኖር አለመሞት ፈልጓልና ዳግም ጭፍሮቹ
ሳይሰለቹ መጽሐፉን በዓለም ዙሪያ ሁሉ እንዲፈልጉ ትዕዛዝ ሰጠ።
እሱም በህይወት እንዲኖር መጽሐፉ እንደሚያስፈልገው አውቋልና
ስለዛች ስለሞቱ ቀን በጭንቀት እና ፍርሀት ውስጥ ሆኖ አሰበ።
በመጨረሻውም ንጉስ ሰሎሞን ይህ መጽሐፍ በልጁ በንጉስ ምኒሊክ
እጅ እንዳለ ተረዳ።

የጭፍሮች አለቆችን ከየሄዱበት ቦታ ሁሉ ዳግም በእልፍኙ
ሰበሰበ። ወደ ልጁ ምኒሊክ ሀገር ኢትዮጵያ እንዲሄዱና ለንጉስ
ለምኒሊክ እንዲሁም ለንግስቲቱ በጠና መታመሙን ነግረው በጊዜ
የፈለገውን መጽሐፍ እንዲያመጡለት እንዲበላ የተገለጸለትን
የመጽሐፉን ስም ነግሮ አዘዘ። የጭፍሮች አለቆችም ፈጥነው ተነሱና
ወደ ኢትዮጵያ ሄዱ። ከዛም ለምኒሊክ እና ለንግስቲቱ ከሰሎሞን
የተላከውን መልዕክት ነገሩ። ምኒሊክ እና ንግስቲቱ እናቱ ሳባም
ይሄን ሲሰሙ ደነገጡ። ከኢትዮጵያ ንጉሥ ሰሎሞን በጥበብ
የደረሰበትን መጽሐፍት ከመጽሐፉ እና ቅርሶች መካከል አፈላልገው
ይዘው ወደ እስራኤል ከብዙ ወታደሮች ጋር ተጓዙ። ሲደርሱ ግን

ሰለሞን ሞቶ እስራኤል በሀዘን ላይ ሆና ጠበቀቻቸው። በእነሱም ዘንድ ጨርቅ መቅደድ ሆነ... ምኒሊክም ሰሎሞን መጽሐፉን ለምን እንደፈለገው አላወቀም። በእስራኤል ቤት አኖረውት። በእስራኤል ድንኳኖች ውስጥም ጨርቅ መቅደዱ በዛ ሀዘኑም ጠና።

ንባቤን ቀጥያለሁ ሀሳቤ ግን አሁንም ሩቅ ነው።

... መልከ ፄዴቅ፣ ሄኖክ፣ኤልያስ፣ ዲዲሞስ፣ ኒቆዲ ና ባኮስ ከሞት ያመለጡበትን መላ ሰሎሞን በጥበቡ ቢደርስበትም በመዘግየቱ ከሞት ለማምለጥ አልቻለም። ይሄን ጥበብ የያዘ መጽሐፍ ከሰሎሞን እረፍት ሞት በኋላ ከኤልያስና ከሙሴ በቀር ማንም በእስራኤል ምድር አላወቀም።" ይላል እየገረመኝ ነበር። ንጉሥ ሰሎሞን ይሄን ሊበላ እና ሊድንበት ያሰበው ሌሎች ከሞት ያመለጡበት ቅዱስመጽሐፍ ከየት እንዳለ ግራ ተጋባሁ። መልከ ፄዴቅ ኤልያስ እና ሄኖክ መሰወራቸውን በመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ባውቅም ስለ ዲዲሞስ፣ ኒቆዲ እና ባኮስ የሚባሉ ሰዎች መሰወር ወይም አለመሞት አላውቅም። ማንበቤን ቀጥያለሁ። አሁንም ብራናውን እያየሁት ነው። ከሰዓታት ንባብ በኋላ አንድ ነገር ላይ ደረስሁ። ቅዱሳን እና የዓለም ጠበብቶች ከሞት ማምለጫ መሰወሪያውን መጽሐፍ እንዳገኙ እና እንደተሰወሩ።

ደቂቃዎች ሲሄዱ ስለተሰወሩ ቅዱሳን እና ስለተሰወሩበት መንገድ ለማወቅ ጓጓሁ። እዚህ መጽሐፍ ላይ የተሰወሩ ቅዱሳን እንዳሉ ሆነው ብዙ ቅዱሳን ከሄኖክ የተላለፈውን እሱ ከሞት ለማምለጥ የተጠቀመበትን ተጠቅመው ለጊዜውም ለሺህ ዓመታት ከሞት እንዳመለጡ። ለማወቅ ችያለሁ። በተቃራኒው መጽሐፉን አንብበው ለመሰወር ከሞት ለማምለጥ የፈለጉት ሰሎሞን፣ ሙሴ እንደሌሎች ቅዱሳን መሰወር እንዳልቻሉ ይናገራል። ግራ ተጋብቻለሁ በሀሳብ አይኔን ከአንዱ ወደ ሌላኛው እየጣልሁ አዕምሮዬን እየመላለስሁ እጠይቃለሁ። ስለተሰወሩ አባቶች ለማወቅ ያለኝ ጉጉት ጨመረ።

እንዴት መሰወር ወይም አለመሞት ቻሉ? የሚለው ጥያቄ ይመላለስብኝ ጀመር።

ሁሉም ሰው ሞትን እንደሚፈራ አውቃለሁ፣ ቅዱሱም እርኩሱም የሞት ቀኑ ያስጨንቀዋል። አለመሞት እና መሰወር ቢለያዩም በጦር፣ በርሀብ፣ በስቃይ መሞት የቱንም ሰው የሆነ ፍጡር ያስጨንቀዋል። ሁሉም ሰው ሞቶ በምድር ትቢያ አፈር ሆኖ ከመኖር አለመሞትን ይመርጣል። የትኛውም በምድር ያለ ፍጥረት እስከቻለ ላለመሞት እና ላለመውደቅ ይጣጣራል።

መጽሐፉን ዘጋሁና ስለ ሞት ማሰቤን ቀጠልሁ። እነዚህ ቅዱሳን አባቶች ለምን ሞትን እንደፈሩት አልያም ሞትን ካልፈሩ ለምን እንደተሰወሩ የመሰወሪያ ሚስጢራቸው ምን እንደሆነ ባላውቅም ሞት ቀላል አለመሆኑን ከዚያም በላይ የሞት መዳኛ ከሞት መሰወሪያ መጽሐፍ በኢትዮጵያውያን እጅ እንደነበር ተገንዝቤያለሁ።

ወደ ራሴ ተመለስኩ እኔ ሞትን ሳስብ መሞቴ ሳይሆን አሟሟቴ ያስጨንቀኛል። ሁሌም እንዴት እሞት ይሆን የሚለው ጥያቄ ውስጤን ይረብሸዋል። አሁን አሁን ኢትዮጵያ ውስጥ እየተስፋፋ እንዳለው ሰዎች እርሀራሄ በማጣት አንገቴን ቆርጠው ስጋዬን በጫጭቀው ይገድሉኝ ይሆን? ህንፃ ተደርምሶ፣ ድንጋይ ወድቆብኝ፣ መኪና ገጭቶኝ፣ በጦርነት የተነሳ፣ ውሃ ውስጥ ሰጥሜ፣ በርሀብ፣ አስፈሪ በሽታ ይዞኝ፣ በአሳት ተቃጥዬ፣እንስሶች በልተውኝ ነውስ ሌላ አሟሟት እሞት ይሆን? ስለሞት ሳስብ በአምሮዬ እነዚህ ይመላለሳሉ። ሁሉም ነገሮች አስፈሪዎች ነበሩ። ያስጨንቃሉ፣ የሰው ሞት ለእራሱ ያለርህራሄ በጎች አርዶ መግደል፣ሰዎች በዘራቸው በእምነታቸው ሲገደሉ እንደማየት፣ዳር ቆሞ በል ግፋ እያሉ ጭፍሮች እና የጭፍሮች አለቆችን እንደማፋጀት አይደለም። ወይንም ሰውን አማራ፣ ትግሬ፣አሮሞ ሌላም በሚል ስም አንጠልጥለን እንደምንሰቅለውም አይደለም። ከሞት በኋላ ፈጣሪ እንደቸርነቱ ህይወት ይሰጠናል። ሆኖም ግን ስለሞት ማሰብ ምን አይነት ከባድ እንደሚሆን ተረዳሁ። ሞትን ፈርተው ከሆነ ቅዱሳን ከዚህ አስፈሪ ነገር ለማምለጥ መለመናቸው እና መሰወራቸው አያስገርምም።

የእግዚአብሔርን ታዓምር ወይም ድንቅ ስጦታ ለማሳየት ከሆነም መልካም ነው:: "ግን እንዴት?" አልኩ ለራሴ...

መጽሐፍት ሞትን አትፍሩ ታጢያትን ፍሩ ቢሉም የትኛውም አይነት ሞት አስፈሪ ነው:: ሰው ደግሞ ይሄን አስፈሪ የሆነ ሞት ሊንሰጭ ግድ ነው:: እኛ ቢላ እንኳ እጃችንን ሲቆርጥ ህመሙ ከባድ ሆኖ የሚያስጨንቀን ሆነን:: ሰዎችን በመግደልና በማረድ ብንሰለጥንም ከሞት ፊት ስንቆም ምን እንደሚውጠን አናውቀውም:: መሞት ባያስፈራ ብዙ ሚሊየኖችን በመግደል የተለማመደው ሂትለር ጠላቶቹ ወደ እርሱ በቀረቡ ጊዜ በፍርሀት ባልተንቀጠቀጠ ነበር:: የኢራቁ መሪ ሳዳም ሁሴን ለሱ በማይመጥን ጉድጓድ ውስጥ ተደብቆ ለስምንት ወር የቆየው ሞትን ፈርቶ አይደለምን? ሞት ባያስፈራ ኑሮ የጆሴፍ ስታሊን ቀኝ እጅ ላቬርኒቲ ቬሪ የስንት ሺህ ሰው ደም በእጁ እንዳልፈሰሰ እሱ ሞት ፊት ሲቆም አድኑኝ እያለ በለቅሶ አይለምንም ነበር:: መንግስቱ ሀይለማሪያም ከሀገሩ ሳይሆን ከሞት ነው የሸሸው:: ሌሎች ብዙ ሰዎች ይሄን ሲያደርጉ ታይቷል:: እና እነዚህ የተሰወሩ ጥቂት ሰዎች ከዚህ ሞት የሚያስቀር የሚሰውር ነገር እንዴት አግኝተው ሊተርፉ ቻሉ? ግራ ያጋባል:: የማነበው መጽሐፍ እንደሚለው ሁሉም ከሞት የተሰወሩት እኔ ከዚህ በፊት እንደማስበው ሳይሆን የህይወት መጽሐፍ /ዕጸ-ህይወትን/ አግኝተው ቃሉን በማንበብ ለሆዳቸው በመብላታቸው ነበር:: በተቃራኒው ደግሞ ይሄን ቢያውቁም ቀድመው መድሃኒቱን ስላላገኙት የሞቱ አሉ:: ብዙዎች ደግሞ ስለዚህ መጽሐፍ መኖር እንኳን አያውቁም:: በዚህ ምክንያትም ይህንን መጽሐፍ ለማወቅ ጓጓሁ:: ማንበቤን ቀጥያለሁ...

ከሰዓታት በኋላ ወደ አባ ባህሪ እሄዳለሁ...

ሁለት

ከአንድ ቀን በፊት

ባህር-ዳር ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ግንቡ ጥግ ነበርኩ። አካባቢውን ተመለከትሁት ጸጥ ረጭ እንዳለ ነው። ሞቃት አየር ይነፍሳል። መነኮሳቱ ከኔ ቀድመው ለጸሎት ተነስተው ነበር። አሁንም ርህቡ አለቀቀኝም። ምግብ ከበላሁ ሁለት ቀን ሆነኝ። ቢያንስ ሌሊት ስላልረበሸኝ ተመስገን አልሁ። ለብሼው ያደርሁትን የተበጫጨቀና በቆሻሻ ያደፈ ቡትቶ ልብስ አስተካክዬ በላዬ ላይ በመደረብ ፀጉሬ እና ፊቴ ሳይስተካከል ወድቄ ካደርሁበት ባዶ መሬት ተነስቼ ቆምሁ። በሰላም እና በጤና ጠብቆ ላሳደረኝ አምላክ ምስጋናን በማቅረብ በሰላም እንዲያውለኝ ደግሞ ጸሎት ማድረስ የዘወትር ተግባሬ ነበርና ፊቴን ወደ ቤተ-ክርስቲያን መልሼ ቀልቤንና ሀሳቤን ሰብስቤ ጸሎቴን በቃሌ ማጉተምተም ቀጠልኩ። በእንደዚህ አይነት ሁኔታ ከሰላሳ ላላነሰ ደቂቃ ቆየሁና በጸሎት ያሳለፍኋቸውን ሰላሳ ደቂቃዎች ለሰጠኝ ፈጣሪ ዳግም ምስጋና አቅርቤ መሬት ላይ ተቀመጥሁ። ሆዴ ባዶ ነው። ሁለቱን ቀን ሙሉ ያልበላሁት ወደ ሆቴሎች ሄጄ መለመን ባለመቻሌ እና በእጄም ምንም ገንዘብ ስለሌለ ነበር። ከጊዮርጊስ ቤተ-ክርስቲያንን ተጠግተው የሚኖሩ አባቶችንም እንዳልለምን በእጃቸው ትርፍ የሆነ የሚያጋሩት ምግብ ላይኖራቸው ይችላል ብዬ አሰብሁ። ቤተ-ክርስቲያኑ የሄድኩና የተቀመጥኩት ትላንት ከቀኑ ሰባት ሰዓት አካባቢ ነበር።

እዚህ ላሉ ሰዎች አዲስ ነኝ። አሁንም ባህር ዳር ጸጥ ረጭ እንዳለች ነች። ጸሎት ከጨረስሁ በኋላ ብዙ ደቂቃ ሳይቆይ ቅዳሴ ተጀመረ። ምግብ ስላለመብላቴ ማሰብ ትቼ ወደ ስራዬ ልሰማራ

ተሰናዳሁ። በመንገዱ ማንም ሰው ሲወጣና ሲወርድ አይታይም። ባህር ዳር ማታ ማታ እስከ አራት ሰዓት ወጭ ወራጅ ይበዛባታል። ከአራት ሰዓት በኋላ ግን እስኪነጋ ጸጥ ረጭ ትላለች።

"ተመስገን ፈጣሪ ፀጋህ አይጓደል። ሰላም እንዳሳደርኸኝ በሰላም አውለኝ። በሰራኸው ህንጻ ላይ የተዘራ የተሰማራውን ከፉ ነገር ከላዬ ላይ ጣል" አልሁ።...

ሰዓቱን ተመለከትሁት አስራ ሁለት ተኩል ሆኗል። አላማዬ ባይሳካም ትላንት ምሽት ጀምሮ ከምፈልጋቸው አባቶች ጋር ማውራት ጀምሬያለሁ። ተመለከትኋቸው የማዳበሪያ ከረጢታቸውን እግራቸው ስር አስቀምጠው ፀሎት እያደረጉ ነበር።

አይኔን መለስኩ ባህር ዳር በደቂቃዎች በተሻለ አኳሃን ከእንቅልፏ እየነቃች ያለች ትመስላለች። ሰዎች ከአንዱ ጥግ ወደ አንዱ ጥግ እንቅስቃሴ ጀምረዋል። ሁለቱ አባቶች ግን አሁንም ግንቡን ተጠግተው ፀሎት እያደረጉ ናቸው።

ከሁለት ቀን በፊት ነበር ከጎንደር ከተማ እነዚህ አባቶች ዘንድ ወደ ባህር ዳር የመጣሁት። ከመጣሁ በኋላ ከጊዮርጊስ ቤተ-ክርስቲያን አካባቢ አልጠፋሁም። የመጣሁበት ምክንያትም ይኸው ነበር።

እነኝህ አባቶች እጅ የጥንት የብራና መጽሐፍት እንደሚኖሩ የተለያዩ ሰዎችም መጽሐፍትን ሊገዙ ወደ እነሱ እንደሚሄዱ ከእነሱ አልያም የሚገዟቸው ሰዎች ከገዟቸው በኋላ ከመሰወራቸው በፊት እንድነጥቅና በእጄ እንዲገባ በቅዱስ ቅርስ አፈላላጊዎች ማህበር መሪዎች ታዝጌ ነበር።

ከጎንደር ዩኒቨርስቲ ማራኪ ካንፓስ እየወጣሁ ሳለ ነበር ስልክ የተደወለልኝ።

"ሄሎ አባ ባህሪ" አልኋቸው።



"አቤት ልጄ" መለሱልኝ ከዛም የደወሉበትን ምክንያት ነገሩኝ። መጽሐፉ ከእነዚህ አባቶች መካከል በአንዳቸው እጅ እንዳለ መረጃ ነገሩኝ። መረጃው በከፊል ትከከል መሆኑን አውቄያለሁ። ከዚያ በኋላ ነበር መጀመሪያ ወደ አባ ባህሪ በመሄድ ስለጉዳዩ ለማረጋገጥ የሞከርሁት። እንዴት አድርገን ይሄን ምንነቱ ያልታወቀ ቅርስ ወይም መጽሐፍ እንዴት ማስገባት እንዳለብን አሰብን።

ከቀናት በኋላ ማንነቴ ተውጦ የጎንደር ዩኒቨርስቲ የሳይኮሎጅ መምህር ሳልሆን የኔ ቢጤ ጎዳና አዳሪ ሆኜ ወደ ባህር ዳር መጣሁ። ከሄድሁበት ሀሳብም ተመለስሁ...

ሦስት

ምሥጢራዊው መጽሐፍ

ማታ ወደ ጎንደር ጉዞ ጀምሬ የግድ እዛው ማደር ነበረብኝ። ከባህር-ዳር መውጣት ብፈልግም ከአንድ ቀን በፊት ጀምሮ አሁንም ጊዮርጊስ ቤተ-ክርስቲያን አካባቢ ቁጭ እንዳልሁ ነኝ። አባቶች ፀሎት ሲጨርሱ የማዳበሪያ ከረጢታቸውን እንደያዙ መጥተው አጠገቤ ተቀመጡ።

ከጠዋት ጀምሮ እስከ አሁን እዚሁ ነበርሁ። በርከት ያሉ መነኮሳት ከተቀመጡበት አካባቢ ከሁለት አባቶች አጠገብ ብቀመጥም ሰዓታት አልፈው አጠገባቸው ምጽዋት ሊጥልላቸው ካሰበ በስተቀር ለሌላ ጉዳይ ወደ አንዳቸውም የመጣ ሰው አልነበረም ። ትናንትም ቀኑ እንደዚሁ ነበር ያለፈው።

“ተሳስቼ ይሆን?” ስል እራሴን ጠየቅኩ። አባ ባህሪ በእርግጠኝነት ስለእነዚህ አባቶች ነው ያወሩኝ ጠቋሚዎቼም ቢሆኑ ያሳዩኝ እነሱኑ ነው። እርግጠኛ ለመሆን ሞከርኩ። ትክክል ነበርሁ...

ጥቂት በከተማ የሚኖሩ መነኮሳት በገዳማት በየዱሩ ያለ አውሬ፣ ነፍሳቱን፣ ጫካውን ያሉበትን ድንጋያማ፣ በእባብ፣ በጊንጥ እና በዘንዶ የተሞላ ቦታ እያለሙ ዓለምን አሸንፈው ስለ ህዝቡ እየጸለዩ ከመኖር ይልቅ የከተማ ቤተ ክርስቲያንን ግድግዳ ተጠግተው በድካምና በዓለም መሸነፍ ውስጥ ሁነው መጽሐፍት፣ ቅርስን እየሰረቁ እየሸጡ ሲያልፍም የሰውን እጅ እያዩ በልመና ይኖራሉ። አልኩና መልሼ ከመፍረዴ በፊት እራሴን ለመመልከት ሞከርሁ። ድህነት እና ማጣት ምን ያህል እንደሚያሰቃይ የረሳሁ መሰለኝ። ፈጣሪ ማንም ሰው ሲራብ አይቶ ዝም እንዳይል ጠየቅኩት።

ጊዮርጊስ ቤተ-ክርስቲያንን የተጠጉ እነዚህ አባቶች እኔን ያዩኛ ትናንት ነበር። ባገኙኝ ሰዓት ግን ለምን እዚህ ተቀመጥህ? ለምንስ መጣህ? ምንስ እያደረግህ ነው? አላሉኝም። እንደነሱ የቸገረኝ እና ከፈጣሪ አጠገብ እርቆ ለመኖርም የማልሻ ቤተ ክርስትያንን ላለመራቅ አጠገባቸው የተቀመጥሁ መስያቸው ይሆናል። ከአለባበሴ በስተቀር ጤናዬ የተሟላ ወጣት ነኝ። በዚህ ምክንያት ሳይሆን አይቀርም በጥቂቱም ቢሆን እነሱን መጠጋቴን አልወደዱትም። ቢሆንም ተነስ እንዳይሉኝ ፈሩ። ምናልባት ተነሳ ቢሉኝ የምናገራቸው አሊያም ለዱላ የምጋበዝ መስሏቸው ይሆናል። አብሬያቸው ተቀምጬ ብዙ ሰዓታት አለፉ።

ወደ እኔ እና እነ አባ አጠገብ የሚመጣው ሰው አልፎ አልፎ ነው። ለእኔ ገንዘብ የሚጥልልኝ። ምናልባት እንደ አባቶች አላሳዝን እና መስራት አለብህ ብለው አስበው ይሆናል። "ሲጀመር እጄን ለመዘርጋት፣ ለልመና አልተቀመጥሁም" አልሁ ለራሴ ግን ይሄንን ማን ያውቃል። ከመጣሁበት ቀን ጀምሮ አልፎ አልፎ ብቻ ነበር እነ አባ ስለ እኔ የሚጠይቁኝ።

ቆይተው ግን ይመክሩኝ ገቡ፦

በዚህ እድሜዬ ልመና ውስጥ መሰማራቴ መልካም እንዳልሆነ፣ ነገ ከነገ ወዲያ ሱስ ሊሆንብኝ እንደሚችል፣ ሰርቼ መብላት እንዳለብኝ ነገሩኝ። አልፎ ተርፎም ማዕድ አብሬ እንድበላ አድርገው በአንድ ቀን የቤተሰብ ያህል አቀረቡኝ። ምናልባት ስለ እኔ አውርተው ሀሳቤን ሊያስቀይሩኝ አልያም ስለ እኔ በጥልቀት ሊያውቁ አስበው ይሆናል። ስምንት ሰዓት አለፈ። ምንም አዲስ ነገር የለም። ስለ ቅርስና መጽሐፍት አያወሩም። እዚህ ተቀምጬ ቀናት በማለፋቸው ተስፋ ቆርጬ ከአካባቢው ልሄድ ሳስብ...

አንዱ መነኩሴ አንድ ነገር ሲናገሩ ሰማሁ። ደነገጥ አልሁና የመሄድ ሀሳቤን ለጊዜው በመሰረዝ ለመቆየት ወሰንሁ።

እራሳቸው ላይ አዳፋ ቢጫ ቆብ ያጠለቁት እና ጺማቸው አልፎ አልፎ የበቀለው፣ በቆባቸው ስር ነጭ ጸጉራቸው ወርዶ የሚታየው፣ አይናቸው የፈዘዘ እና እርጅና ያጎበጣቸው የሚመስሉት መነኩሴ አንድ ሰው ከጊዮርጊስ ቤተ-ክርስቲያን ሲወጣ እያዩት አጠገባቸው ላሉት መነኩሴ እየጠቆሙ...

"ተመልከተው የቤተ ክርስቲያንን መጽሀፍ እየሰረቀ እና እያሰረቀ የሚሸጠው ሰው ይሄ ነው::" አሉ

"ምን ይሄ ሰውዬ! ለዛ ነው አንዳንድ ሾላካ አባቶች እግር ስር የማይጠፋው?" ጠየቁ ጺማቸውም ጸጉራቸውም የተንዠረገገው ሌላኛው መነኩሴ የጺማቸውን ፀጉር እየዳበሱ:: ሾላካ ማለታቸው ግን ትንሽ አላስማማኝም የተናገሩት እሳቸውን ጨምሮ መሆን አለበት:: የሰው ልጅ እራሱን ሳይሆን ሰዎችን ብቻ ነው የሚመለከተው:: እራሱ አጥፊ ሆኖ የሰዎች ነገር ገኖ ይታየዋል:: እነዚህን አባቶች ጨምሮ በድብቅ የቤተ-ክርስቲያን ነዋያትን እያወጡ ለሌሎች አሳልፈው የሚሰጡ ብዙ መነኮሳት እንዳሉ አውቃለሁ:: እኔም የምፈልገው እነሱን እና ከነሱ መሰል እጅ ያሉ የቤተ-ክርስቲያን ነዋያትን ነው::

"አዎ ከብዙ አባቶች ጋር ተገናኝቶ በየቤቶታቸው ያሉ የጥንት መጽሐፍት እንዲሸጥላቸው ይጠይቁለታል:: ከዛም በጥሩ ዋጋ ለሌሎች ሰዎች ይሸጥላቸዋል:: ደግሞ መቅሰፍት እንኳ አይፈራም ታቦት እራሱ ይሸጣል ይባላል::" አሉና ለጓደኛቸው ተናገሩ ... ለእሳቸው ከታቦት ውጭ ያለው ሌላው ቅዱስ ነዋይ ከቁብ የሚቆጠር አይመስልም::

"ስሙን ታውቀዋለህ ታድያ?" አሉ መነኩሴው

"አይ አላውቀውም ግን ሁሌም ከቤተ-ክርስቲያን አይጠፋም:: እኔም አንዴ ሲቸግረኝ 'መፍትሔ እስራኤል' የሚባል መጽሐፍ ሸጬለት ነበር:: ምነው ፈለግኸው?" ጠየቁ:: ያኔ ስለ ሰውዬው ትንሽ

ነገር ያወቅሁ መሰለኝ፡፡ ሰውዬውን በደንብ ለማስተዋል ሞከሬያለሁ፡፡ አንድ እግሩ ያጠረ እያነከሰ የሚጓዝ ፊቱ ቀይ ወገቡ የሸበተ ሰው ነው፡፡ ምናልባት ሌላ ቀን እሱኑ ፍለጋ እንደምመጣ እርግጠኛ ሆንሁ፡፡

"አዎ እኔም አንድ እኔ ዘንድ ብቻ ያለ የሚመስለኝ የጥንት መጽሐፍ እጄ ላይ አለ፡፡ መጽሐፉ 'ዝራስኤል' የሚል ርዕሰ አለው፡፡ እሱን መጽሐፍ በደህና ዋጋ የሚገዛኝ ከሆነ ላንተም የድርሻህን እሰጥሀለሁ፡፡" አሉ ደንግጬ አፈጠጥሁ በጉጉት አይኔ ሊወጣ ደረሰ፡፡ በጀሮዬ ሰጥቼ በጥሞና እያዳመጥኋቸው ነበር፡፡ ሰዎችን ሸላካ ሲሉ ቆይተው እራሳቸው የባሱ ሆኑ፡፡ አሁን የተላከሁበት ቦታ ትክክል ስለመሆኑ አረጋግጫለሁ፡፡

አባ ስለሚያወሩት መጽሐፍ ከዚህ በፊት ሰምቼ አውቃለሁ፡፡ መጽሐፉ ከሁለት ሺህ ዓመት በፊት ነው የተጻፈው፡፡ ከዘመናት በፊት ጅምሮ ነገስታት እንደሚጠቀሙበት አውቃለሁ፡፡ ኢትዮጵያ በጊዜው ግዛቷ የት እንደሆነ በእርግጠኝነት ባላውቅም በዚያ ዘመን ስለነበረችው ኢትዮጵያ ያወራል፡፡ መጽሐፉን ከዚህ በፊት ለዓመታት ብፈልገው እና ባስፈልገውም ላገኘው አልቻልኩም ነበር፡፡ ዛሬ እንዴት ተገኘ? አሳቸው እድሰ እንዴት ገባ? ለራሴም ጥያቄ ሆኖብኛል፡፡ ደግሜ ግራ በመጋባት እንዴት የሚል ጥያቄ እራሴን ጠየቅሁ፡፡ መልስ የለኝም... እንዴትስ በገንዘብ የማይተመን መጽሀፍን አሳቸው በርካሽ ዋጋ ሊሸጡት ወደዱ? የመጽሐፉን ይዘት አያውቁ ይሆን? አላውቅም ግራ በመጋባት ውስጥ ሆኜ ተመለከትኳቸው፡፡ እኛ አባቶቻችንን በመናቃችን መጽሐፎቻቸውን ልንጠቀምበት ስላልቻልን እያየናቸው ከእጃችን ሲወጡ በትቂት ገንዘብም ለባዕዳን መጠቀሚያ ስናደርጋቸው ማዬት ሁሌም ያማል፡፡ አዎ ያማል! መቼ ይሆን የምንነቃውና ልባችን የሚመለሰው?

"ይገዛሀል መጽሐፉ ግን ስለምንድን ነው የሚያወራው?" አሉ ሌላኛው አባት... ወደ ጨዋታቸው ተመለስሁ፡፡

"ኧረ ቆይ ላሳይህማ እንዲያውም ይገርሞሀሉ፡፡ መጽሐፉ ደግሞ የትም ቦታ የለም የጥንት መጽሐፍ ነው፡፡" በማለት በእኔ በኩል ያሉት አባት እግራቸው ስር ያለውን ጓዛቸውን የሸከፉበት ትልቅ የማዳበሪያ ከረጢት ውስጥ እጃቸውን በመላክ መጽሐፉን አወጡት፡፡ ፍንጭ በማግኘቴ የተደሰትሁትን ያህል እኔ እዚህ ማዳበሪያ ውስጥ ይቀመጣል ብዬ አለማሰቤ አናደደኝ፡፡ ቀድሜ ባውቅ ስራዬን በሌሊት እጨርስ ነበር፡፡ "አሁን ዕቃው ማዳበሪያው ውስጥ ስለመሆኑ እርግጠኛ መሆኔ እንጂ ጊዜው አልረፈደም" አልሁ ለራሴ ...

አጠገባቸው ላሉት አባት ማሳየት ጀመሩ፡፡ አይኔን አፍጥጬ ብሌኑ ጉድጓዱን ለቅቆ እስኪወጣ መጽሀፉን ተመለከትሁት፡፡ አባ ለመነኩሴው ጓደኛቸው አሳይተው ሲጨረሱ መልሰው ማዳበርያው ውስጥ ጨመሩት፡፡ ስለመጽሀፉ ይዘት ያወሩ ጀመር፡፡ የሚያወሩት እኔ ከማውቀው የተለዬ አልነበረም፡፡ የጥንቷ ኢትዮጵያ ለብልጽግናዋ፣ ለልማቷ እንዲሁም ለአንድነቷ አንድ አማራጭ ሊኖራት እንደሚገባ የሚያሳይ መጽሐፍ ነው፡፡ ንጉሶቿም በፈጣሪ እንዲደገፉ የሚናገር ነበር፡፡ ኢትዮጵያ በፖለቲከኞች ፍጭት እና ግጭት ሳይሆን በፈጣሪ በረከት እና ቸርነት የምትኖር ሀገር ነች፡፡ በማህበራዊ በኢኮኖሚ ዘርፍ ልታድግ የምትችለው በሳይንሳዊ የጥበብ መንገድ ሳይሆን በመንፈሳዊ የጥበብ መንገድ እንደሆነ ያትታል፡፡ የመንፈሳዊ ጥበብን መንገድ ልትይዝ እንደሚገባ ይመክራል፡፡ መንፈሳዊ የጥበብ መንገድ ምን ማለት እንደሆነ በስፋት ይገልጻል ነበር ያሉት፡፡ ስለ መጸሐፉ አያውቁ ይሆናል የሚለውን ሀሳብ አነሳሁ፡፡

"ታድያ ለምን ይሸጡታል?" ዳግም ራሴን ጠየቅሁ ምናልባት ድህነት ይሆናል፡፡

"እውነት የኢትዮጵያ አለማደግ ምክንያቱ ይሄ ይሆን?" አልሁኝ ለራሴ፡፡ ጠልቀን ስለ መንፈሳዊው ጥበብ አለማወቃችን አልያም ደግሞ የሳይነሳዊውን መንገድ ብቻ መከተላችን ከተፈጥሮ ጋርም

ስለማንታገል ሁለቱንም ጨብጠን ለመሮጥ በምናደርገው ጥረት ይሆን ከነበርንበት ወደ ኋላ የቀረን? ግራ እጋባለሁ:: አባቶቻችን በመንፈሳዊ ጥበብ ብቻ ተመርተው ብዙ ነገሮችን ሰርተው ዛሬም ድርስ የዓለም ጠበብት ይነጋገርባቸዋል:: አክሱም፣የፋሲል ግንብ፣ ላሊበላ እና ሶፍ ኡመር ዋሻ እንዴት ተሰሩ? በምን ጥበብ? ለኛ ለዛሬዎቹ ጥያቄ ብቻ ነው የተረፈን:: እኛስ መንፈሳዊ ጥበብም ርቆን፣ ሳይንሳዊው ጥበብ ሳይገባን እስከ መቼ እንዘልቅ ይሆን? አልሁ:: አንዳንዴ ወደ ሁለቱም ልባችን እየተመላለሰ መካከል ላይ ሆነን እየተደናበርን ይሆናል:: ይሄ መጽሐፍ ብዙ የኢትዮጵያ መሪዎች ሲያነቡ እና ሲጠቀሙበት እንደኖሩ ሲወራ ሰምቻለሁ:: የእሁኖቹ መሪዎች እንዴት እንዳጡት አላውቅም ይሄ መጽሐፍ እኒህ ደካማ መነኩሴ ዘንድ ግን በምን መልኩ ኖረ? መልስ የለኝም...

ደቂቃዎች ተጉዘው ሰዓት ተባሉ:: ትንሽ ተጣደፍኩና ከተቀመጥሁበት ተነሳሁ:: ሁለቱ አባቶች አንድ ላይ እኔን ለመጥራት እየተቻኮሉ ይመስል::

“ልጄ” አሉኝ

“አቤት” አልኩ ደንገጥ ብዬ። እየተፃደፍሁ...

“ወዴት ልትሄድ ነው የተነሳህ አሁን እኮ ሊመሽ ነው” አሉኝ:: ሌላ ነገር ይሉኝ ይሆን ብዬ ፈርቼ ነበር:: ሰዓቱ ገና ነው... እየተደናበርሁና እየተጨነቅሁ...

“መጣሁ መጣሁ እመለሳለሁ::” አልሁኝ::

“እሽ በቶሎ ና አትራቅ” አሉ አንደኛው አባት እሽታዬን ከአንገቴ በላይ ቀና በማለት ገልጬ በፍጥነት ከአጠገባቸው ራቅኩ:: ጉዞዬን መናኸሪያ ከማድረጌ በፊት ልብሴን ወደ ምለውጥበት ደበቅ ያለ ቦታ አመራሁ:: ተጣደፍኩ በመንገድ እየተጓዝሁም ልቤ በደስታ እየደለቀ አረፍት ነሳኝ:: ከሁለቱ አባቶች ዓይን መራቄን ሳረጋግጥ በደስታ ሮጬ ተፈተለኩኝ:: ከእነሱ ዓይን እስከርቅ ግን በስጋት እና

በጭንቀት ውስጥ ተወጥሬ ነበር። በጣም ደስ አለኝ። ከእነ አባ እና ከጊዮርጊስ ቤተ-ክርስቲያን እጅግ በጣም እርቄያለሁ። ከመንገዱ ውጭ በጣና ዳር አንድ ዛፍ ጥግ ሄድሁ ቆሜም የያዝሁትን ኩርቱ ፌስታል በፍጥነት ከፈትኩት። እጄን ሰድጄ አንድ መጽሐፍ አወጣሁ። ከእኒያ አባት መጽሐፍ ሰርቄያቸው ነበር። አባ መጽሐፉን አውጥተው ለሌላኛው አባት ካሳዩ በኋላ መልሰው በእኔ በኩል ባለው የማዳበሪያ ከረጢት ሲያስቀምጡት በማየቴ በድብቅ በምላጭ ቀድጄ ነበር ያወጣሁት። መጽሐፉን ስወስድ ሁለቱም አባቶች በወሬ ተጠምደው ነበር። እሳቸው የወሰዱት ከቤተ-ክርስቲያን እና ከውስጥ ካሉ አባቶች ነውና እኔም ከእነሱ ሰርቄ በመውሰዴ አልተጸጸትሁም። ድሮ ጀምሮ ይሄን ሳደርግ ነበር። በአንድ ቀን ውስጥ ማሳካት ከሚገባኝ ነገር በላይ እንዳሳካሁ ውስጤን ተሰማኝ። ከሺህ አመታት በፊት ተጻፈ የተባለ "ዝራስኤል" የሚል ርዕስ ያለው መጽሐፍን በማግኘቴ ደስ አለኝ። ከፌስታሌ መጽሐፉን አውጥቼ ገልጬ ከማየቴ በፊት ደጋግሜ ሽፋኑን እየተመለከትሁ ሳምኩት። ከላይ የተጻፈ ነገር አልነበረም።

መጽሐፉ ይዘት ከጸሎት መጽሐፍ የማይበልጥ ነበር። ቀድሞ ያየሁት መጽሐፍ ስለመሆኑ ተጠራጠርሁ። ልከፍተው ሞከርሁ። መጽሐፉ አልከፈትልኝ አለ። እንዴት እንደዚህ ሆነ? እርግጠኛ የሆንኩት እንዳልገባኝ ብቻ ነው ከአባ የወሰድሁትም ያንን ቀድሜ ያየሁትን መጽሐፍ አልነበረም። ተናደድኩ አላማየን ሳላሳካ መቅረቴ አበሳጨኝ ተመልሼ ወደ እነርሱ መሄድ አልችልም ነበር። ደጋግሜ ልከፍተው እና ላየው ሞከርሁ። አልሆነም...

ጥራዙን ልቀደው ሞከርሁ። አልቻልሁም ተናድጄ በሀይል ወረወርሁት። ጥራዙ ከድንጋይ ጋር ተጋጭቶ ወደቀ። በዚህ ጊዜ ከውስጡ ብዙ ወረቀቶች ተበታትነው መሬት ወደቁ ግራ ያጋባል። ወረቀቶቹን ከያሉበት መሰብሰብ ጀመርሁ። አጫጭር የብራና ወረቀት ጽሁፎች ነበሩ። የተጻፈውም በአማረኛ እና በግእዝ ነው።

በተመለከትሁት ነገር ደንግጫለሁ... ቀድሞም ጥራዙን ለመክፈት አልቻልሁም ነበር:: ባላስብሁት መልኩ ግን በንዴት ሰወረውረው ተከፈተ::

የወረወርሁትን የመጽሀፉን ወረቀቶች መልሼ ሰብስቤ ሰጨርስ በፌስታሌ ውስጥ አስገባሁ:: ከዛም ፈጥኜ ጉዞዬን ወደ አንድ ደቡቅ ያለ ቦታ አደረግሁ:: በአካባቢው ብቻዬን መሆኔን እና ማንም ሰው እንደማያየኝ ሳረጋግጥ የለበስሁትን ቡትቶ ልብስ አውልቄ በፌስታል ውስጥ የነበረ ጥቁር ሱፍ ልብስ አውጥቼ ለበስኩ:: ፊቴንም አባብሼ እና ጠራርጌ ከላዬ ላይ የነበረን ቆሻሻ ነገር ሁሉ አስወገድኩ:: አምሮብኝ ወደ ከተማው ተመለስሁ::

ከተማ ላይ ስደርስ ንግድ ባንክ ፊት ለፊት ወዳለ የኢ.ቲ.ኤ.ም. ማሽን በመሄድ ብር ለማውጣት ሞከርሁ:: ዛሬም እንደ ትናንቱ ኤ.ቲ.ኤም ማሽኑ አይሰራም:: ፌስታሌን እንዳንጠለጠልሁ ወደ ባንክ ገብቼ ገንዘብ አወጣሁ:: አሁን ማንም ሰው እንደ እብድ አይቆጥረኝም:: አለባበሴ ጥሩ የሚባል ነው:: ከባንክ እንደወጣሁ ምግብ በልቼ ጉዞዬን ወደ መናኸርያ አደረግሁ::

ከጎንደር የመጣሁት ለዚህ ስራ ነበር:: ያየሁትን የፈለግሁትን መጽሐፍ ባላገኝም ሌላ መጽሐፍ በመያዜ አልከፋኝም:: በፍጥነት ወደ ጎንደር መመለስ ስለነበረብኝ ወደ መናኸሪያ ገብቼ ሚኒባስ መኪና ላይ ተሳፍሬ ጉዞዬን ወደ ጎንደር ከተማ አደረግሁ:: ምናልባት ነገ ከነገ ወዲያ ወደ ሁለቱ አባቶች ዳግም ተመልሼ መሄድ ባልችል ከተመለከትሁት ሰው ዘንድ መጽሐፉን ወደ ፊት ላገኝ ስለምችል አክሲማሮስ መጽሐፉን ለአባ ሰጥቼ የገጠመኝን እነግራቸዋለሁ::

አራት

ጎንደር፣ ከባህር-ዳር መልስ

ጎንደር ከተማ እንደገባሁ የትም ሳልሄድ ከተከራየሁበት ቤት ውስጥ ሻውር ወስጄ፣ ራት በልቼ፣ ከመነኩሴው የወሰድሁትን የብራና የጸሎት የሚመስል ትንሽ መጽሐፍ ማንበብ ጀመርሁ። እኒያ አባት አብሬያቸው ብቆይ ብዙ ጥንታዊ መጽሐፎች እጃቸው ላይ እንደማገኝ አስቤያለሁ። ለዚህም ነው አንድ መጽሐፍ ብቻ ይዤ ከእነሱ በመራቄ እስከ አሁን የምበሽቀው። ያም ሆነ ይህ አይቼው ሰምቼው የማላውቀውን የጥንት መጽሐፍ በማግኘቴ ደስተኛ ነኝ። መጀመሪያ ልነጥቃቸው ያሰብኩትን መጽሐፍ ዛሬ ባላገኘውም የሆነ ቀን ተመልሼ ወደ እነሱ ሄጄ ባልወስደውም ያ! መጽሐፎችን በየቦታው እየዞረ እንደሚገዛ የተነገረለት ሰው ከገዛው እና በእጁ ካስገባው ሰውየውን ስለማውቀው ከሱ እንደማገኘው እርግጠኛ ነበርሁ።

የወሰድኩት መጽሐፍ "የህይወት መንገድ" ይላል። የተጻፈበት ዘመን ባይታወቅም ከመቶ አመታት በላይ እንደሚሆነው በእርጅናው ይገመታል። የተፃፈውም በብራና ላይ ነው። የጸሐፊው ስም መጽሐፉ ሽፋን ላይም ሆነ የመጀመሪያ የውስጥ ገጹ ላይ የለም። ቢሆንም ከርዕሱ ታች አንድ በጉልህ የተጻፈ ነገር ነበር። 'ላለመሞት ከፈለግህ የሞት መድሃኒት /ዕፀ - ሕይወት/ መጽሐፉን ብላ እግዚአብሔር ፍላጎትህን አይቶ ከሞት ያድንህል' ይላል። ለአባ ባህሪ ለመስጠት አልፈለግሁም። ቀድሜ ራሴ መጽሐፉን ላነበው ፈለግሁ። ለዚህም ነበር ገልጬ እያየሁት ያለሁት።

"... ንግስት ሳባ የንጉስ ሰሎሞንን ጥበብ ለማዬት ኢየሩሳሌም ደርሳ ከመጣች በኋላ ዘጠኝ ወር ሲሞላ ወንድ ልጅ ወለደች። ስሙም 'ምኒሊክ' ተባለ። ትርጉሙም የብልህ ሰው ልጅ ማለት ነበር።

....ንጉስ ቀዳማይ ምኒሊክ ከተወለደ በኃላ ሀያ ዓመት ሙሉ በእናቱ ቤት እትብቱ በተቀበረበት ሀገር ኢትዮጵያ በክብር እና በልዩ እንክብካቤ አደገ። ሃያ አመት ሲሞላው ከእናቱ እርቆ ወደ አባቱ ንጉስ ሰለሞን ሀገርና ቤት እስራኤል ተጓዘ። በዛም በአባቱ ቤት በንጉስ ሰለሞን ፊት በክብር በሞገስ መንፈሳዊ ጥበብን፣ አስተዳደርን፣ ህግን እየተማረ አንድ አመት ብቻ እንደቆየ በሃያ አንድ አመቱ የእስራኤል ሹማምንት ከአባቱ ጋር የነበረውን ቀረቤታ ተመልክተው "ስልጣናችንን ሊወስድ ይችላል በአባቱ እግር የሚተካው እሱ ይሆናል፤ ስለዚህ ከዚህ ሊሄድ ይገባል" በሚል ቀኑ። በሸንጓቸው ቁጭ ብለውም ተማከሩበት። ለንጉስ ሰለሞንም ቅሬታቸውን አቀረቡ። ንጉሱም የቅናታቸውን ምንጭ ስላወቀ እና ስለተረዳ ልጁ ምኒሊክ ለንግስና አለመምጣቱን ተናገረ። የአይሁድ ቀሳውስት፣ አባቶች እና ልዑላን አልሰሙትም። እናቱ ከእስራኤል በህዝብ እና በስፋት የምትበልጥ ሀገር እያስተዳደረች መሆኑን ነገረ። እነሱ ግን አላመኑም። በየድንኳኑም አመጻ እና ተቃውሞ ነገሰ። በመጨረሻም የእነሱ ፍላጎት እንዲሆን ሁሉም የእስራኤል አስራ ሁለቱ ነገዶች ሹማምንት የአይሁድ ካህናት ከበኩር ልጃቸው ምኒሊክ ጋር ወደ ኢትዮጵያ ከላኩ ከእስራኤል በዚያው ዓመት ወደ እናቱ ምድር እንደሚልከው ተናገረ። አይሁዳዊያንም በንጉሱ ሀሳብ ተስማሙ። ንጉስ ሰሎሞንም የእነሱን ሀሳብ ለመፈጸም ወሰነ። ንግስተ ሳባ ልጁ በአባቱ ፊት በጥበብ ሊያድግ ወደ አባቱ ሀገር ሄዶ እንጅ ትልቅ ግዛት ሀገር አላት። የምኒሊክ ወደዚያ መሄድ አላስደሰታትም ነበር። እንደተባለውም ሆነ...

ምኒሊክ ከአባቱ ሀገር ወደ ኢትዮጵያ ገስግሶ እየመጣ በነበረ ጊዜም በአጠገቡ የኢትዮጵያ የጦር መሪዎች እና ጭፍሮቻቸው ከአስራ ሁለቱም የእስራኤል ነገድ የዘር ግንድ የሚመዘዙ ከአብርሃም፣ ከይስሀቅ፣ ከያዕቆብ ዕርስት አንድ ሺህ ሁለት መቶ የሚሆኑትን

የበኩር ልጆች ጨምሮ ሌሎች ሶስት መቶ አስራ ስምንት በአዛርያስ የሚመሩ ሌዋውያን ካህናት አብረውት ነበሩ።።

ከሶስት ወራት ቀደም ብሎ ነበር ምኒሊክ እናቱ ወደ ምትመራት ሀገር ኢትዮጵያ ለመሄድ ከእስራኤል ከመነሳታቸው በፊት... ንጉሰ ሰለሞን ልጁን ምኒሊክን እሱ ሰሎሞን የሚያመልከው የአይሁዳዊያን አምላክ እንዲጠብቀው እና ለዘለዓለም ከህዝቡ ጋር እንዲሆን በሰሎሞን መንግስት፣ በእስራኤል ህዝብ እና በእግዚአብሔር መንግስት የዓለማዊ ስርዓትንና የመንፍሳዊ ህግ ስርዓት የሚያስረዱ መጽሐፍትን፤ የንግስናን እንዲሁም የቤተ መቅደስ ህጉንም የሚያስተምሩ፣ የንግስና ስርዓቶች እና የአምልኮ ስርዓቶች እንዲቀጥል የሚያደርጉ ቅርሶች እና መጽሐፍት ሙሉ ቅጅዎች ከቤተ መንግስትም ከቤተ መቅደስም እያሰባሰቡ እንዲያዘጋጁ ከእስራኤል የበኩር ልጆች መካከል ተመርጠው የታዘዙት።።

ይሄም ትእዛዝ አብረውት ወደ ኢትዮጵያ በሚሄደው በሌውያዊው አዛርያስ የቤተ መቅደሱን ስርዓት መፈጸሚያ ቅርስ እና መጽሐፍት ቅጅዎች በኢትዮጵያ እንዲተገበር እንዲይዝ፣ እንዲሁም በአለማዊው የአስተዳደር ስርዓት ረገድ ሌሎች አስራ ሁለቱን ነገዶችን የተወከሉ ሰዎች በሶሎ መሪነት እንዲያዘጋጁ ተደርጓል።። ይሄንንም በትጋት ፈጽመዋል።። ሌዊያዊው አዛርያስ እና በሶሎ የተመሩ ሌሎች ከአስራ ሁለቱ የእስራኤል ነገዶች የተውጣጡ ሰዎች ስራቸውን በፍጥነት እያከናወኑ ነበር።። አዛሪያስ ከተወለደባት እና ከኖረበት እስራኤል ይልቅ ለሚሄድባት ሀገር በማድላቱ እንደተባለው በቤተ መቅደስ ያሉ ቅርሶች እና መዛግብትን እንዲሁም መጽሐፎች ሲያዘጋጅ ቅጅውን ብቻ ሳይሆን እውነተኞችንም ቅርሶችን እና መጽሐፍትን ከዚህም አልፎ በእስራኤል ከጥቂት ሰዎች ውጭ በብዙ ህዝብ የማይታወቁትንም መጽሐፍትና ታቦተ ህጉን ጨምሮ አሰናዳ።። ይሄም ስራ እንደተባለው ከእስራኤል ከመነሳታቸው በፊት ባለው በሶስት ወር ውስጥ ተጠናቀቀ።።

ጉዞ ወደ ኢትዮጵያ ከእስራኤል ማዘት ተጀምሮ ከአራት ወር በኋላ ኢትዮጵያ ድንበር ላይ አየደረሱ ነበር። በቅያም አዛርያስ የሰራው ሰራ ትክክል እንዳልሆነ ገባው። ማድረግ ያልነበረበትን ነገር ማደረጉ ሀሊ.ናውን አየመቀሰው ይሞግተው ጀመር። በመጨረሻ የታዘዘውን ባለማድረጉ አውነት አሸንፈውና አዘነ። አዕምሮውን አጀጉን አስጨነቀው። ይሄንን ማድረጉ ትክክል አለመሆኑን ከተረዳ ቀናቶች ቢያልፉም ትክክል ነኝ በሚል አራሱን አያታለለ ነበር። ቀይ ባህርን እንዳለፉ ግን ሁሉንም በልቡ ያለውን ነገር ሊናገርው ወሰነ። እስከዚያ ሰዓት በመደበቁም የሚደርስበትን ለመቀበል ዝግጁ ሆነ። በቀኑም ከረጅም ጉዞ በኋላ በሚያድሩበት ሁሉ ከእስራኤል የጫኑትን እህል ለማብሰል እና ለአዳር የሚመች ቦታ መርጠው ለልዑሉ እና ለቅዱሳን ቅርሶች የሚሆን ድንኳን እየጣሉ ያድራሉ። በቀኑም ከረጅም ጉዞ በኋላ ቦታ መርጠው ለአዳራቸው የሚሆን ድንኳን ዘርግተው የአምልኮ ስርዓቱን አከናውነው፣ ጨርሰው እየበሉ፣ እየጠጡ እና እየተጫወቱ ባሉበት ሰዓት ሌውያዊው አዛርያስ ይሄን ተናገረ። ሁሉም ሰው የተናገረውን በዝምታ እና በግርምት ሰማ። ጽላቱን ጨምሮ ዋና ዋና ቅዱሳን ቅርሶችን እንዲሁም በእስራኤል የተዘነጉ የተረሱ ቅርስ እና መጽሐፍት ዋናውን ይዞ በነሱ መልክ የተቀረጹትን አስቀምጦ ወደ ኢትዮጵያ እንደመጣ ይሄም ትክክል አለመሆኑን ጥፋት እንደሰራ በራሱ ላይ መሰከረ።

ምኒልክ ይሄን ሲሰማ እሳት ለብሶ እሳት ጎርሶ የተሰራው ስራ አግባብ አለመሆኑን በመግለፅ በዛው ቀን ዕቃዎችን በብዙ ዝሆኖች እና አጋሰሶች ይዞ ወደ ኢትዮጵያ እየተጓዘ ስለሆነ መልሶ እነዚህን መጽሐፍት እና ቅርሶች ወደ እስራኤል ለመላክ ስለማይችል አዛርያስን ገሰፆ። ለአባቱ ስለሁኔታው በመልክተኞች ሊልክ ተዘጋጀ።

ምኒልክ በዛው ባረፈበት ቦታ ከመጡት ከእስራኤል አስራ ሁለቱ ነገዶች መካከል ጎበዛዝቱን መርጦ ነገ ከሌሎች የሱ ጠባቂ

ኢትዮጵያዊያን ጭፍሮቹ ጋራ ወደ እስራኤል እንዲመለሱ እና ለአባቱ ጉዳዩን እንዲያደርሱ በማዘዝ መልዕክቱን ይጽፍ ጀመር።

መልዕክቱም እንደዚህ የሚል ጭብጥ ነበረው።

"ንጉሰ ነገስት አባቴ ሰሎሞን ሆይ እንዴት ነህ? እኔ፣ የእስራኤል ልጆች እና ልጆችህ ደህና ነን። አሁን የጉዟችን መገባደጃው ላይ ደርሰናል። በዚህ ወቅት አንድ ስህተት እንደተሰራ አወቅኩ።" በማለት ጀምሮ ኢትዮጵያ እየሄደ ያለው ቅዱሱ ቅርስ መጽሐፍት መዘግብት ሙሉ በሙሉ ቅጅው ሳይሆን ዋናው መሆኑን ከዛም በላይ በእስራኤላውያን የተረሱ የተዘነጉ ቅዱሳን መጽሐፍትን ዝርዝር ጨምሮ ይዞ እየሄደ እንዳለ። ይሄም የሆነው በስህተት መሆኑን እሱ አባቱን ለማታለል የሰራው ስራ እንዳልሆነ ቅዱሳን ንብረቶችን አሁኑኑ ለመመለስ ቢፈልግና ቢያስብም ስለሚያስቸግር መመለሻው ስለ ሚከብድ ሌላ ጊዜ ንጉስ ሰሎሞንን ከልቡ ይቅርታ ጠይቆ እንደሚመልስ ይገልጽ ነበር።

በጠዋቱ ይሄን መልዕክት ይዘው ወደ እስራኤል በሚገሰግሱ መልዕክተኞች እንዲደርስ ምኒልክ አዘዘ። የተፈጠረው ነገርንም በእሱ እና በጭፍሮቹ ዜና መዕዋል ጸሐፊው እንዲጻፍ አብረው ለተከተሉት አጃቢ ኢትዮጵያውያን እና ከሱ ጋር ለመጡት የእስራኤል አንድ ሺህ ሁለት መቶ የበኩር ልጆች እንዲሁም ለሶስት መቶ አስራ ስምንቱ ሌውያዊያን ካህናት በአዋጅ መልክ እንዲነበብ አስደረገ። በዚህ ምክንያት ሁሉም ወደ ኢትዮጵያ እየመጡ ባሉት እስራኤላዊያን እና ኢትዮጵያውያን ድንኳን ውስጥ ይሄ ነገር ታወቀ...

ከልዑል ምኒልክ ተልከው ወደ እስራኤል ንጉሥ ሰሎሞን መልዕክት እንዲያደርሱ ከታዘዙ መልዕክተኞች ውጭ ያሉት የእስራኤል እና የኢትዮጵያ ልጆች ከልዑሉ ጋር ወደ ኢትዮጵያ አከሱም ከተማ ተጓዙ። አከሱምም ህዳር ሃያ አንድ ቀን በደረሱ ጊዜ የልዑሉ እናት ንግስተ ሳባን ጨምሮ ሌሎች የበዙ ሰዎች ወጥተው

በደስታ ተቀበሏቸው። በአከሱም ከተማ በተጣሉ ድንኳኖች ሰርም ተደገሰ ሰውም ደስ የሚያሰኘውን ምግብ በላ መጠጥም ጠጣ።

ከቀናት በኋላ ንግስተ ሳባ ከእስራኤል ከሰሎሞን ቤተ-መቅደስ ከልጇ የመጣውን ነገር ሁሉ አወቀች። ታቦቱን ጨምሮ እስራኤል ውስጥ የማይገኝ ቅርስ እና መጽሐፍት በማየቷ ደስ አላት። ደስታዋ እጥፍ ድርብ ሆነ። ልዑሉ በእውቀት እና ጥበብ ከእሷ ልቋልና ንግስናዋን ለእሱ ለምኒሊክ አስረከበች። ያመጡት ቅርስና መጽሐፍት ሁሉንም ከበፊት ጀምሮ ለግዛቷ እና ህዝቦቿ እንዲሁም ለራሷ ትፈልጋቸው ነበር ። ልጇንም በአንድ ዓመት ውስጥ ባከናወነው ተግባር አደነቀች። ልጇ ግን የአባቱን መልስ ሲጠባበቅ ነበር።

ምኒሊክ ኢትዮጵያ በገባበት ዓመት በኢትዮጵያ ምድር የመጀመሪያው የሰሎሞን ስርወ መንግስት መሪ ሆኖ ቢነግስም ለንጉሥ ሰለሞን ንብረቶችን ሊመልስ እና አባቱን ሊያይ ያሳለፋቸውን ሁለት ዓመታት ወደ እስራኤል አልተጓዘም።

***

በ37 ዓመተ-ምህረት የጌታ መልአክ ፊልጶስን ተነሥተህ በደቡብ በኩል ከኢየሩሳሌም ወደ ጋዛ ወደ ሚያወርደው ምድረ በዳ ወደ ሆነ መንገድ ሂድ አለው፤ ተነሥቶም ሔደ፤ እነሆም "ህንደኬ" የተባለች የኢትዮጵያ ንግሥት አዛዥና ጃንደረባ የነበረ በገንዘቡም ሁሉ የሰለጠነ አንድ የኢትዮጵያ ሰው ሊሰግድ ወደ ኢየሩሳሌም መጥቶ ነበር፤ ሲመለስም በሠረገላ ተቀምጦ የነቢዩን የኢሳይያስን መጽሐፍ ያነብ ነበር፤ መንፈስም ፊልጶስን ወደዚህ ሠረገላ ቅረብና ተገናኝ አለው፤ ፊልጶስም ሮጦ የነቢዩን የኢሳይያስን መጽሐፍ ሲያነብ ሰማና "በእውኑ የምታነበውን ታስተውለዋለህን?" አለው፤ እርሱም "የተረጐመልኝ ሳይኖር ይህ እንዴት ይቻለኛል?" አለው፤ ወጥቶም ከእርሱ ጋር ይቀመጥ ዘንድ ፊልጶስን ለመነው፤ ያነበው የነበረው የመጽሐፉ ክፍል ይህ ነበረ፥ "እንደ በግ ወደመታረድ ተነዳ፣ የበግ ጠቦትም በሸላቹ ፊት

ዝም እንደሚል እንዲሁ አፉን አልከፈተም፤ በውርደቱ ፍርዱ ተወገደ፤ ሕይወቱ ከምድር ተወግዳለችና ትውልዱንስ ማን ይናገራል::" ጃንደረባውም ለፊልጶስ መልሶ እባክህ ነቢዩ ይህን ስለማን ይናገራል ስለ ራሱ ነውን ወይስ ስለሌላ? አለው፤ ፊልጶስም መናገር ጀመረ፤ ከዚህም መጽሐፍ ጀምሮ ስለ ኢየሱስ ወንጌልን ሰበከለት:: በመንገድም ሲሔዱ ወደ ውሃ ደረሱ፤ ጃንደረባውም እነሆ ውሀ እንዳልጠመቅ የሚከለክለኝ ምንድነው?" አለው:: ፊልጶስም "በፍጹም ልብህ ብታምን ተፈቅዷል" አለው፤ መልሶም "ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ አምናለሁ" አለ:: ሰረገላውም ይቆም ዘንድ አዘዘ፤ ፊልጶስና ጃንደረባው ሁለቱም ወደ ውሀ ወረዱ፤ አጠመቀውም፤ ከዚያም የእግዚአብሔር መንፈስ ፍሊጶስን ነጠቀው ተሰወረው:: ዳግም አላየውም::

ጃንደረባው ባኮስ ግን በመንፈስ ቅዱስ ተሞልቶ ወደ ኢትዮጵያ ደስ እያለው ተመለሰ...

ከቀናት በኋላ አክሱም እንደደረሰ ስለገጠመው ሁሉ ለቤተሰቡ ተናገረ:: መንፈስ ቅዱስም ተሞልቷልና ቤተሰቡን እና በአጠገቡ ያሉ ሌሎች ሰዎችን በፍቃዳቸው አስተምሮ እሱም ከፊሊጶስ ባገኘው ክህነት መሰረት አጠመቃቸው:: የነገስታት የመንግስት አባል ነበርና በነገስታት ፊትም ቁሞ ስለ ሆነው ሁሉ በድፍረት አወራ:: የክርስቶስ ፍቅር ገብቶት ነበርና ስራውን ትቶ የክርስቶስ አገልጋይ በመሆን ለሰው ሁሉ ሊያስተምር ወደ ኢትዮጵያ ጫፍ ሄደ:: በኢትዮጵያ ሰሜን፣ ደቡብ፣ ምዕራብ እና ምስራቅ አስተምሮ በመጨረሻም አባይ ምንጭ መገኛ በቅርብ እርቀት የመጀመርያውን የድንኳን ቤተ-ክርስቲያን ተከለ:: ከገነት ምንጭ በሚፈልቀው የአባይ ውሀም በአካባቢው የሚኖሩና ከሌሎች አካባቢዎች የሚመጡ ብዙ የስጋ እና የነፍስ ህመማን ይፈውስ እና ያጠምቅ ነበር:: በዚህም በምድሪቱ ስሙ ናኜ በጊዜው በሌዊያውያን ካህናት እና በተወሰኑ

ኢትዮጵያውያን ተቀባይነትን አጥቶ የነበር ቢሆንም እየቆየ በሁሉ ዘንድ ተቀባይነትን አገኘ።

ጊሻ ጊሻ ጊሻ ጊሻ... ሀይቅ አካባቢ ባኮስ ለብዙ ዓመት ኖሯል።" የሚል በተደጋጋሚ መጽሐፉ ላይ ተጽፎ ተመለከትሁ። አተኩሬ ሳይ ድንገት መብራት ጠፋ። ብራናውን ዘጋሁና አስቀምጬ በሀሳብ ተወጠርሁ። ከተቀመጥሁበት ሳልነሳ ስለ ጊሻ ሀይቅ ማሰብ ጀመርሁ።

ጊሻ ሀይቅ ካነበብሁት እና ከዚህ በፊት ከማውቀው አንጻር ያለው በቀድሞው አከላለል ስርዓት ጎጃም ክፍለ ሀገር አገው ምድር ሲሆን በአሁኑ አዊ ዞን ውስጥ ነው። በቲሊሊ እና ኢንጅባራ/ኮሶበር/ ከተሞች መካከል ከባህር ዳር ወደ አዲስ አበባ ሲመጡ በግራ መስመር የሚገኝ ሀይቅ ነው። አሁን የሚጠራው ዘንገና ሀይቅ እየተባለ ነው። ቀድሜ እራት በልቼ ተሰናድቼ ስለነበር ወደ አልጋዬ ሂጄ የሌሊት ልብስ ሳልለብስ ጫማዬን ብቻ አውልቄ ተጋደምሁ።

ከባህር ዳር ስመለስ ሁለት የጥንት መጽሐፍት ይዤ ነበር። አንደኛው አሁን እያነበብሁ ያለሁት "የህይወት መንገድ" የሚል መጽሐፍ ሁለተኛ አክሲማሮስ የተሰኘውን መጽሐፍ ነበር። "አክሲማሮስን" ነገ ለአባ ባህሪ ልሰጣቸው ነው። መጽሐፉም ብዙ ቦታዎች መኖሩን አውቃለሁ። የጥንት ከመሆኑ የተነሳ ነው ከሰዎች የወሰድሁት እንጅ ሀሳቡ ያው የማውቀው ብዙ ሰው እጅ ያለው ነው። ይሄን እያነበብሁት ያለውን መጽሐፍ ግን ማንበብ ከጀመርሁ በኋላ ለሰዎች መስጠት አባም እንዲያዩት አልፈለግሁም። ምክንያቴ ደግሞ ይሄን መጽሐፍ አይቼው ስለማላውቅ እና ስለመጽሐፉም ስላልሰማሁ ነበር። ብዙ ዓመታት መጽሐፍን በማፈላለግ አሳለፍሁ ግን መጽሐፉን አላውቀውም። ስለ መጽሐፉ አንብቤ፣ ተመራምሬ ለማወቅ ከመሻቴ የተነሳ ጓጓሁ። በቀጣይ ምን እንደሚሆን ባላውቅም ያገኘሁትን ይሄን መጽሐፍ እኔው ጋር አስቀርቼ አለመስጠትን

ልተገብር እና ልዋሻቸው ነበር። ይሄን ሳደርግ ደግሞየመጀመሪያየ ነው።

“አሁንም እያሰብሁ ያለሁ ስለሱ ነው። ይሄ መጽሐፍ ከዘንገና በጥንት ስሙ ‘ጊሻ’ ሀይቅ ጋር ምን አገናኘው? ዘንገና ሀይቅ በጥንት ስያሜው ‘ጊሻ’ መባሉን የሚያውቁ ጥቂት ጽሁፎች እና ሰዎች ይሆናሉ... ስለዚህ መጽሐፉ ጥንታዊ መሆን አንዱ ማረጋገጫዬ ይሄ ነው።” አልሁ በውስጤ። መጽሐፉን ስላልጨረስሁት ምን ሀሳብ በውስጡ እንደያዘ ልረዳ አልቻልሁም ነበር። ጠዋት ነግቶ እስካነብ ጓጉቻለሁ። ስለ ዘንገና ሀይቅ ማሰብ ቀጠልሁ...

ማሰብ... ማሰብ... ማሰብ...

ከአመታት በፊት የአስራ ሁለተኛ ክፍል ተማሪ እያለሁ አባ ባህሪ ከአንድ አባት ጋር ዘንገና /ጊሻ/ ሀይቅ አካባቢ ወደ ሚገኘው ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን ልከውኝ ነበር። በወቅቱ ወደ ዘንገና ስሄድ የመጀመርያዬ ቢሆንም ብዙ ሰዎች አልፎ አልፎ በሰርግም በመዝናናትም ሰበብ ወደ ቦታው ሄደው ያውቃሉ። እኔም ብሆን ብዙ ሰዎች በአካባቢው ስለሚኖሩ ቀዬው የሚጠፋኝ አልመሰለኝም። ከጎንደር ባህር-ዳር ከዛም ወደ ቲሊሊ ጉዞ ጀመርሁ። በሀገር አቋራጭ ባስ ከሶስት ሰዓት ያላነሰ መንገድ ተጉዤ ዘንገና ሀይቅ የሚገባበት ቦታ ስደርስ ለረዳቱ ዘንገና ሀይቅን ቀድሜ አላውቀውም ብየው ስለነበር እንደደረስሁ በቅንነት ነግሮ ውረድ አለኝ። ከቀኑ አራት ሰዓት አካባቢ ነበር።

ጉዞዬን ከአስፓልት እርቄ በዛፎች ዳር እና ዳር በተጋረደው የውስጥ ለውስጥ ቀጭን መንገድ አደረግሁ። የሚነፍሰው አየር ሰላም ይሰጥ ነበር። ንጹህም ነው። ጥቂት መንገድ ተጉዤ ደረስሁ። ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን እና ዘንገና ሀይቅ በቅርብ እርቀት የሚተያዩ ናቸው። ወደ ቤተ ክርስቲያኑ ከመሄዴ እና አባ ሰላመ አብን ከማግኜቴ በፊት መጀመሪያ ሀይቁን አይቼው ስለማላውቅ ለማየት

ፈለግሁ። የቤተ ክርስቲያኑን መግቢያ ትቼ ወደ ሀይቁ መስመር መንገዱን ይዤ ጉዞዬን ቀጠልሁ።

ሀይቁም በዛፎች የተከበበ ሲሆን ስፋቱ ከሌሎች ሀይቆች ጋር ሲወዳደር ይሄን ያህል ትልቅ የሚባል አልነበረም። ሲያዩት የሚያምር እና የሚያስደንቅ የተፈጥሮ ውበት አለው። ወደ ሀይቁ በሚወስደው መንገድ ውስጥ ሲጓዙ ደስ የሚል አየር ይነፍሳል። ሀይቁ አጠገብ ደረስሁ። እንደሌሎች ሀይቆቻችን በቆሻሻ እና በውሃ ላስቲክ ተሞልቶ የተበከለ አይደለም። ንጽህናው ደስ የሚያሰኝ እና ግቡብኝ ግቡብኝ የሚል ነበር። አተኩሬ ባየሁት ቁጥር እጅግ ደስ አለኝ።

በሀይቁ ውበት እጅግ ተስቤ ቀስ እያልሁ ልብሴን ሳላወልቅ ወደ ውሃው ውስጥ እገባ ጀመር። ውሃው እስከ ጉልበቴ ደረሰ እያየሁት አልተሰማኝም... ብዙ ሳልጓዝ አንድ ቁምጣ ሱሪ ለብሶ ከላይ ፎጣ የተከናነበ ሰው ቦቲ ጫማውን አድርጎ እየሮጠ ወደ ሀይቁ እየገባ በጩኸት ይጠራኝ ጀመር። መጀመሪያ ግራ ተጋብቼ ነበር። ምን ሊያደርግ ገባ እንዴትስ ጠራኝ? ስለሱ መጣራት እንጅ ስለሚለው ትኩረት አልሰጠሁትም። ጉዞዬን ቀጠልሁ... የሚጣራው ሰው ጩኸቱን ቀጠለ።

“አንተ ሰውየ... አንተ አንተን እኮ ነው?” እየጮኸ ተከተለኝ። አሁንም በማስተዋል ሆኜ አልሰማሁትም። ልቤ ውሃው ላይ ነበር። ሰውየው በድነጋጤ ውስጥ ሆኖ እሩጦ መጥቶ ገፍትሮ ወረወረኝ። ባነንሁ... ወደ አዕምሮዬ ተመለስሁ። እየጎተተም ከውሀው አወጣኝ። ተከትየው ስወጣ ለምን አላልሁትም። ሰውየውን አስተዋልሁት... ከአንዱ ጎጆ የመጣ ገበሬ ይሆናል። በአስተዋይነት ፊቱ ቅርጫም ብሏል። ድህነቱ ቢያኮስሰውም በልቡ ያለው ደግነት እና ድፍረት ፊቱ ላይ በርቶ ይታያል። ከሄድሁበት የሀሳብ ጉዞ ወጥቻለሁ። እኔም ቢሆን ከቆይታ በኋላ ነበር ጨርሼ ሀይቁ ውስጥ እየገባሁ እንደሆነ የገባኝ። ዘንገና ሀይቅን እየከፈልሁ ስጓዝ ልቤን ምን ሰልቦት እንደሆነ አሁን ድረስ አላውቅም።

ሰውየው እኔን ከሀይቁ ካወጣ በኋላ ሰለምሄድበት ቦታ ጠየቀኝ። ወደ አንድ አባ ሰላመ አብ የሚባሉ አባት ተልኬ መልዕክት ላደርስ ወደ ቅዱስ ገብርኤል ቤተ-ክርስቲያን እየሄድሁ እንደሆነ አጫወትሁት። መልዕክቱን ሳላደርስ ሙቼ እንደነበር አጫወተኝ። ከሀይቁ ዳር ጫማዬን አውልቄ ውሃውን እያፈሰስሁ ሱሪየን ለማድረቅ እየሞከርኩ ነበር። እሱም ቦቲው ውስጥ ያለውን ውሃ እያፈሰሰ... ትንሽ ሀይቁ ጥግ ቆየንና ጉዞ ጀመርን።

በጉዟችን ለምን ወደ እዚያ እንደሄድሁ ጠየቀኝ።

"እንዴት ወደዚያ ሄድህ?" አለኝ

"ሀይቁን አይቼው ስለማላውቅ ላይ ነበር።" ነገርሁት እሱ ግን እየተገረመና ነገሬ አልፎ እያናደደው።

"ውስጡ ገብተህ ነው እንዴ የምታየው?" አለኝ እና ቀጥሎም...

"መዋኘት ትችላለህ?" ጠየቀኝ

"አልችልም" መለስኩለት ተገርሞ ተመለከተኝ።

"እዛ ውስጥ ጅኒ እንዳለ አታውቅም? ደግሞስ እንደዚህ አይነት ሀይቅ ላይ እኩለ ቀን መሄድ እንደማይገባ ሳይገባህ ቀርቶ ነው።" አለኝ። ቀጥሎም ብዙ ሰዎች እዚህ ውስጥ ገብተው እንደሞቱ አሁንም ብቻቸውን እኩለ ቀን የሚመጡ እና የሚገቡ ሰጥመው እንደሚቀሩ፣ እንዲያውም አሁን አሁን ተለምዶ ሰዎች ለሰርግ እና ለተለያዩ ዝግጅቶች እየተጠቀሙበት እንጅ በአፈ-ታሪክ ይሄ ቦታ ከሺህ አመታት በፊት ምንም ውሀ ያልነበረው መሬት የነበረ ሰዎች በሀጥያታቸው ምክንያት ንፍር ውሃ ፈጣሪ ላያቸው ላይ እንደዝናብ በማዝነቡ ከታችም ምድር ሸሽታ ውጣቸው ብዙ ሰዎች እንደተቀበሩ አወራኝ።

"ከዘመናት በፊት ይሄ ሀይቁ ያለበት ቦታ ሰዶምና ገሞራ ነበር ማለት ነዋ?" አልሁ። ጥያቄዬን ለመመለስ የተቻኮለ የሚመስለው ሰውዬ...

"ይላሉ እንግዲህ እግር እራሱን አያክ አይደል የሚባለው። እኛ አልኖርንበትም በዘመኑ የነበሩበት ከተናገሩ መስማት ማመን ነው። እኛ አለኝ ትክክል አልሁ እግር እራሱን አያክም። ከነበሩት ሰዎች ይልቅ ስለ ነበረው ነገር እኛ አናውቅም።

ቤተ-ክርስቲያኑ አቅራቢያ ስንደርስ ሁለታችንም ተሳልመን። ከሞት ስላዳነኝ አመስግኘው እኔ ወደ ቤተ-ክርስቲያኑ ግቢ እሱ ወደ ሚሄድበት ቦታ ተሰነባብተን ተለያየን።

በደቂቃዎች እንደሚተዋወቅ ሰው ብዙ ተጫወትን። አባ ባህሪ የላኩኝን መልዕክት ላደርስ አባ ሰላመ አብ ጋር ተገናኘሁ። አባ ሰላመ አብ ፊታቸው በፀጉር የተሞላ ከተወለዱ ጀምረው ፀጉራቸውን የተላጩ የማይመስሉ ሲሆኑ በፀጉራቸው የተነሳ ምን አይነት ፊት እንዳላቸው ባላውቅም ደከም ያሉ፣ ረዥም፣ ትህትናን የተላበሱ ሰው ናቸው። መልዕክቱን ካደረስሁ በኋላ ስለ ዘንገና በጥንት ስሙ /ጊሻ/ ሀይቅ ጠየቅኋቸው። ህይወቴን የታደገኝ ሰው ያለኝ ነገር ትክክል እንደሆነ አባም በራሳቸው አፍ አወሩኝ። በእውነት ገረመኝ... ከአባ ጋር ስናወራ አባ ስለላኩኝ ጉዳይ ስነግራቸው ቆይተን ተለያየን

ከሄድሁበት ሀሳብ ተመለስሁ ባልገመትሁት መንገድ ከነዚያ ሁለት አባቶች እግር ስር የወሰድሁት ጥቅል መጽሐፍ እያሳሰበኝ፣ እያስገረመኝ ነበር። ስለዚህ መጽሐፍ በውስጡ ስለያዛቸው ነገሮች ለማወቅ ጓጓሁ። ከእስራኤል ቤተ-መንግስት እና ቤተ-መቅደስ የመጡ ንዋያት እንዲሁም ስለ ጃንደረባው ባኮስ የሚገልጥ ትንሽ ጉዳይን አጠቃሎ አንብቤያለሁ። 'ሁሉም እስራኤል ውስጥ የነበሩ ቅርሶች እና መጽሐፍት ኢትዮጵያ ውስጥ ነው የሚኖሩት ማለት ነው?' አልሁና ራሴን ጠየቅሁ። መልሱን ግን አላውቅም። ቀዳማይ ንጉሥ

ምኒልክ ራሱ ያመጣቸውን ንዋያት መልሶ ስለመውሰዱ የሚያሳይ መረጃ እስከ አሁን አላነበብሁም ነበር። ለነገሩ አንብቤ አልጨረስሁም።

እንዴት ይሄ መጽሐፍ እጄ ገባ? ሌላ ጥያቄ ምናልባት ከእስራኤል ወደ ኢትዮጵያ የመጡ ቅርሶችን መጽሐፍትን ፈጣሪ ፈቅዶልኝ ሊጠቁመኝ ይሆን? ርዕሱ ደግሞ የህይወት መንገድ ነው የሚለው ነውስ "ስለ ሞት መድሃኒት ስለ አለመሞት /መሰወር/ "በመጽሐፉ" ውስጥ ይኖር? አልገባኝም። መጽሀፉ የሚሰወርብኝ መሰለኝ። በስልኬ መብራት አብርቼ ከተጋደምሁበት አልጋ ተነስቼ ካስቀመጥሁበት ቦታ በመሄድ አየሁት። አለ አልተሰወረም

"ተመስገን" አልሁና አስቀምጬው ተመልሼ ወደ አልጋዬ ሄጄ ተኛሁ። ነገ ጠዋት ከእንቅልፌ እንደተነሳሁ አነበዋለሁ።

"ዘንገና ሀይቅ ምን እንዳለ እናያለን እስኪ" አልሁ። ግራ በመጋባት ውስጥ ሁኜ ከሀሳብ ሳልወጣ ደስታ ይሁን ሌላ ነገር እያስጨነቀኝ ቆይቶ እንቅልፍ ወሰደኝ።

አምሥት

አዲስ ምዕራፍ

አሁንም መኖሪያ ቤቴ ውስጥ ተቀምጬ ያን መጻሐፍ እያነበብሁ ነበር። ሰዓታት አልፈው ሰባት ሰዓት ተኩል ሲሆን አባ ባህሪን ለማግኘት ወደ ቤተ-ክርስቲያን ለመሄድ ተነሳሁ። ሙቀቱ ሰውነትን በሚያነድበት ሰዓት ላይ በጡንቻማ ሰውነቴ ጥቁር ሱፍ ሱሪ ከላይ ነጭ ሸሚዝ ለብሼ ከቤት ከወጣሁ በኋላ ባጃጅ ተሳፈሬ ለተወሰኑ ደቂቃዎች ተጓዝሁ። ከባጃጅ ወርጄ ራመድ፣ ራመድ እያልሁ ወደ ገብርኤል ቤተ-ክርስቲያን አጥር ግቢ ደረስሁ። አማትቤ ቤተ-ክርስቲያንን ሰላም ለኪ በማለት ወደ ውስጥ ገባሁ። ሙቀቱ እራቁት ቢሄዱ እራሱ የሚያቃጥል ነበር። ሰባት የእግር እርምጃ የሚሆን ርቀት እንደተጓዝሁ ፊት ለፊት የሚታየውን የህንጻ ቤተ-ክርስቲያኑን መስመር ትቼ ወደ ግራ መስመር ባለች ቀጭን መንገድ ጉዞዬን ቀጠልሁ። አካባቢው በድሮ ዘመን ትላልቅ ለሚባሉ ሰዎች ለመቃብር የተሰሩ ፎቅ የጭቃ ቤቶች መስመር ነበር። እነዚህ ቤቶች በአሁኑ ጊዜ ለቆሎ ተማሪዎች መኖሪያ፣ መማሪያና እና እዚያው ለሚኖሩ የቤተ-ክርስቲያኑ አባቶች እና መሪዎች መኖሪያ ሁነው ያገለግላሉ።

በምሄድበት አቅጣጫ ከቤተ-ክርስቲያኑ ፊት ለፊት ትይዩ ወዳሉት ወደ እነዚህ ቤቶች በሚወስደው በር ተጓዝሁ። የአባ ባህሪ እና የቆሎ ትምህርት የሚማሩት ተማሪዎች መኖርያና የመማሪያ ቦታም እዚህ ነው። በሩን አልፌ ወደ ውስጥ ገባሁ። አባ የቆሎ ተማሪዎቻቸውን ከሚያስተምሩበት አንድ አነስተኛ አዳራሽ ጀርባ ሌላ በር አልፌ ወደ ውስጥ ገባሁ። ብዙ ተማሪዎች ፎጣቸውን ለብሰው ዕርስ በዕርስ ሲማማሩ አንዳንዶቹ እየዘመሩ፣ አንዳንዶች ደግሞ

የለመኑትን ደረቅ እንጀራ ላስቲክ ላይ አስጥተው በፀሀይ ሲያደርቁ እና ባሰጡበት ቦታ ላይ ያለውን ደግሞ በእንጨት ሲያገላብጡ ይታያል። እነሱን ትቼ ወደ አባ ባህሪ መኖሪያ ቤት በሩን አልፌ ልገባ ስል አንድ በአስራዎቹ እድሜ ውስጥ ያለ ወጣት የቆሎ ተማሪ ሱሪውን እየሰፋ የነበረበትን መርፌ እንዳንጠለጠለ ፎጣውን ከጀርባው አዝሎ ፈንጠር ብሎ ከተቀመጠበት በመነሳት እየተመለከተኝ...

"ጋሼ ወደ የት እየሄዱ ነው?" አለና ጠየቀኝ ቆምኩ። ከእኔ በእርቀት ያለ ሌላ የቆሎ ተማሪ ግን አየኝና ከእሱ በተቃራኒ

"ጋሼ መጡ? የአባ ባህሪ የንስሀ ልጅ እኮ ናቸው። አባን ፈልገው ነው የመጡት።" አለ ከመጀመሪያው በእድሜ የሚበልጥ ይመስላል። ከለበሰው ቁምጣ በታች እርቃኑን ያለ ሰውነቱን በእጆቹ እየሞዠለገ። አንቱ ማለቱ የአክብሮት እንደሆነ ስለማውቅ የተነገረው ነገር ትክክለኛነቱን በአውንታ ገለጽሁለት።

"ታድያ ቢሆንም አባ አሁን ነው የተኙት። ስለዚህ ማንም ቢሆን እሳቸውን ማናገር አይችልም። እሳቸው የተናገሩት ይሄንኑ ነው።" አለ ወደ እኔ እየተጠጋ... በየጊዜው አዳዲስ የአብነት ተማሪዎች ስለሚቀላቀሉ ምናልባት አያውቀኝ ይሆናል ብዬ አስቤያለሁ። ለተወሰኑ ደቂቃዎች እኔም ሁለቱን ተማሪዎች እየተመለከትሁ ቆየሁና...

"ግድ የለም እናንተ አሁን ግቡና ጠይቋቸው አባ እየጠበቁኝ ነው አልተኙም። ይልቅስ ከቻልህ ሂድና ደግሰው /ወልደ ሚካኤል/ መጥቷል በልልኝ። ከዛ ይግባ ካሉ እገባለሁ። ካላሉ ደግሞ ተመልሼ ወደ መጣሁበት እሄዳለሁ።" አልሁና አዘዝሁት።

"እየነገርሁህ መሰለኝ አሁን ማንንም አያናግሩም የተኙት በቅርብ ሰዓት ነው። ሌሊቱን ለቅዳሴ ቆመው ነው ያደሩት።" አለኝ እንድገባ ያልፈለገው ወጣት... በውስጤ የተማሪው ቅን አለመሆን እና ደረቅነት

ሊያናደደኝ ስጥተሙተምሁ። አንዳንዴ እንደዚህ አይነት ካር
እንደሚከሰት ረስቸው አልነበረም። ከተቀመጡት ተማሪዎች
የሚያውቀኝ መሆኑን ቀድሞ በንግግሩ የገለጠልኝ ተማሪ
ከተቀመጠበት በመነሳት ፈጠን ብሎ ...

"እኔ ካልተኙ አይሎታለሁ ይጠብቁኝ መጣሁ::" በማለት ወደ
ሌላኛው በር አመራ ወደ ውስጥም ገባ:: በዚህ የተናደደው
አላስገባህም ያለኝ ተማሪ እያጉተመተመ ወደ ተነሳበት ቦታ በመሄድ
ተቀመጠ:: ልብሱን መስፋቱን ቀጠለ... ወደ አባ ባህሪ ግቢ የገባው
ተማሪ ከሄደበት ብዙም ሳይቆይ ዶሎ ተመልሶ መጣ:: ፍጥነቱ
የጠየቃቸው አያስመስለውም::

"አልተኙም መግባት ይችላሉ ነግሬያቸዋለሁ:: ይምጡ
ብለዋል..." አለኝ:: የጠየቀልኝን ተማሪ አመስግኘው ጣደፍ፣ ጣደፍ
እያልሁ ወደ አባ ባህሪ መኖሪያ ግቢ ገባሁ:: የአባ ባህሪ መኖሪያ ጎጆ
ከሌሎች አባቶች ቤት ራቅ ብላ ያለች ሲሆን ዙሪያዋን በተለያዩ ሀገር
በቀል ዛፎች ተከባለች:: በቤቷ ጀርባ ደግሞ መጨረሻው የማይታወቅ
ጫካ ይታያል:: ከዚህ በብዙ ኪሎ ሜትር እርቆ አንድ ከግራኝ
አህመድ ወረራ ቀደሞ የተመሰረተ በዚያ ዘመን ያልጠፋ ታላቅ ገዳም
እንዳለ ሰምቻለሁ::

ግቢው ሰፊ እና ብዛት ባለው ሀገር በቀል ዛፍ ቢታጀብም
እሳቸውም ሆኑ ሌሎች አባቶች የሚኖሩበት ጎጆ ቤት ግን ጠባብ እና
ለምኝታ ብቻ የተሰሩ ነው የሚመስሉት:: አባ ባህሪ ቤታቸው በር
ላይ ወንበር አውጥተው ቁጭ ብለው መጽሐፍ እያነበቡ ነበር::
አጠገባቸው ደረስሁ:: ሰላም አልኋቸው እሳቸው ግን
አልመለሱልኝም:: አስተዋለኋቸው በተመስጦ ውስጥ ያሉ
ይመስላሉ:: ለአንዱው ልጅ እሳቸው ጋር ደርሶ እስኪመለስ እንዴት
ወደ ጥልቅ ንባብ ገቡ? አላውቅም ሲያነቡ በፍጥነት ነበር::
አይናቸውን ከአንዱ ጥግ ወደ ሌላው አንዱ ወስደው ሳይመልሱ አንዱ
ገጽ ያልቅና ሌላ ገጽ ይገልጣሉ:: ከጥንትም ከልጅነታቸው ጀምረው

ሲያነቡ በማደጋቸው ይመስላል ፍጥነታቸው ያስገርማል። ከንባባቸው በወሬ ላስተጓጉላቸው ስላልፈለግሁ መቀመጫ መፈለግ ጀመርሁ። አንድ አግድም የወደቀ ግንድ ተመለከትሁ። እዛ ላይ ሂጄ ተቀመጥሁ። ማንበብ ቀጥለዋል...

አባ ባህሪ እድሜያቸው ወደ ሰማኒያዎቹ የተጠጋ ቢሆንም ብርታታቸው አሁንም አብሯቸው እንዳለ ነው። ቀጥ ያለ እና በእርጅና ያልዘመመ አቋም... ጠንካራ መሆናቸውን ማንም ሰው በእይታ ያውቃል። ለእኔ ከልጅነት እስከ እውቀት እንደዚሁ ናቸው። ቁጥብ፣ የሚናገሩትን የሚያውቁ፣ የተረጋጉ ሲሆኑ። ፊታቸው ጥቁር በመሆኑ የሚማቸው ንፃት እና አንዳንዴም ፈገግታቸው ደስ የሚያሰኝ ገጽታን ያላብሳቸዋል።

አባ ሳያናግሩኝ ብዙ ደቂቃዎችን ካሳልፉ በኋላ ያነቡት የነበረውን መጽሐፍ ሲጨርሱ... መጽሐፉን በቆዳ ከተሰራው ማህደር እየከተቱ እያስተካከሉ።

"መጣህ ልጄ?" አሉ ረጅም ጺማቸውን እየዳበሱ። አጠገባቸው ቁሜ እስከ አሁን መምጣቴን ሳያውቁ ቀርተው ነው? አልሁና መልሼ ምናልባት መጽሐፉ ላይ ሀሳባቸው ስለነበር አላስተዋሉኝ ይሆናል። ከተቀመጥሁበት ቶሎ ብዬ ወደ እሳቸው ሄጄ ጉልበታቸውን ሳምሁ።

"ተው ተው ልጄ ተነስ በል ተነስ" አሉና በእጃቸው ፊቴን እየዳበሱ ባረኩኝ...

"ቆየህ አይደል ከመጣህ?" መልሰው የቀደመውን ጥያቄ ጠየቁኝ መጽሐፉን በቆዳ ከተሰራው ማህደር ውስጥ እየከተቱ።

"ትንሽ ቆየሁ አባ" መለስሁላቸው

"እንዴት ሆነልህ ታድያ የሄድህበት ጉዳይ?"

"ያሰብሁትን ባላገኝም ተሳክቷል አባ" አልኋቸው ዋሸሁ

"አዎ ጎበዝ ጥሩ ነው ልጄ" አሉኝ ለማበረታታት ትንሽ ዝም ብለው ቆዩና ...

"ምን ገጠመህ ታዲያ ልጄ?" እነዚያ አባቶች እጅ አንድ መጽሐፍ እንዳለ ባረጋግጥም ሳወጣው አክሲማሮስ እንደሆነና ሌላ ጊዜ እንደምመለስ ነገርኄቸው:: ደግሜ እየዋሸኋቸው ነበር:: እኔን ስለሚያውቁኝ ሌላ ሰው ሊነጥቃቸው እንዲንቀሳቀስ አወራኄቸው::

"ጥሩ ዋናው መጽሐፉ እነሱ ጋር መኖሩ ማወቅህ ነው:: ምን መጽሐፍ ነው እነሱ ጋር ያለው ታዲያ?" አሉኝ

"ዝራስኤል የሚል የጥንት መጽሐፍ" መለስሁላቸው የመደነቅ ፊት ባያሳዩኝም በንግግራቸው ገብቶኛል::

"መልካም" አሉኝ በቀጣይ እንደምናገኘውም አወራን::

"አንድ መጽሐፍ አለና የጥንት ስለሆነ እሱን ልሰጠዎት ሌላ ትዕዛዝ ካለም ትእዛዝ ልቀበል አስቤ ነው የመጣሁት::" አልኳቸው የውሸቴ መደበቂያ የሆነውን አክሲማሮስ መጽሐፍ እያቀበልኳቸው::

"መልካም ለጊዜው ምንም ትዕዛዝ የለም ስራህን እራስህ ስራ" መለሱልኝ::

"እሽ" አልሁ መጽሐፉን አይተው...

"አክሲማሮስ መጽሐፍ የጥንቱ ነው?" አሉኝ:: መጽሐፉ በቅርብ ዘመን በአማርኛ እየተተረጎመ ለህዝብ የሚሰራጨው ሳይሆን የጥንት መጽሐፍ እንደሆነ አወሩኝ:: የእነዚያ አባቶች ሀሳብ ስለረሱት ደስ ብሎኛል::

አክሲማሮስ መጽሐፍ ከሥነ ፍጥረት መጽሐፍ አንዱ ሲሆን የጻፈውም ቅዱስ ኢዲፋኒዮስ ይባላል:: ቅዱስ ኢዲፋኒዮስ ሲተረጎም ከሳቴ ሚስጥር፣ ገላጭ፣ በር ከፋች ማለት ነው:: የኖረውም በቆጵሮስ ከቤተ ገብርኤል አጸድ አቅራቢያ ነበር:: ከዘመናት በፊት መጽሀፉን ከግእዝ ወደ አማረኛ የመለሱት አባት አባ ሰናይ ሲባሉ መጽሐፉ

የሚያትተውም ስለ ሀያ ሁለቱ ስነፍጥረት ነው። አከሲማሮስ መጽሐፉ ስለ ስድስቱ ቀን ፍጥረታት አሚልቶ የሚፅፍ ሀያ ሁለት ብሎ የሚቆጥር መጽሐፍ ነው። ኢጲፋኒዮስ ወላጆቹ በኦሪት የጠኑ አይሁዳውያን ሲሆኑ እነሱም ከሞቱ በኋላ አንድ ፈላታዎስ የሚባል ክርስቲያን ጋር ተገናኘ። ከዚያ እሱ ሉኪያኖስ ከሚባል መነኩሴ ጋር አገናኘው በዚህ ወቅት እሱም መነኩሴ መሆን ፈለገ። አብሮት ሲቆይ ከአንድ ኢሊዎስን የሚባል መነኩሴ ጋር አገናኘው ከእሱም የቤተ-ክርስቲያን ህግና ስርዓትን፣ የምንኩስና ህግን፣ ተምሮ መነኮሰ። ታላቅ ታምራትን ይሰራ ጀመር። ሰይጣን ያወጣ፣ ሙታን ያስነሳ፣ ምንም በሌለበት ምድረበዳ ውሀ ያፈልቅ ነበር። በቆጵሮስ እስከ ኢጲስ ቆጶስነት የደረሰ ሲሆን በህይወት ዘመኑ ብዙ ድርሳናትን ጽፏል። ከነዚህ መጽሐፍትም መካከል አንዱ ይሄ አከሲማሮስ መጽሐፍ ነው። በማለት ስለ መጽሐፉም በጥልቀት አወሩኝ። እኔም ቢሆን አሚልቼ እና አስፍቼ ባላውቀውም በትንሹ ስለመጽሐፉ እና ቅዱስ ኢጲፋንዮስ አውቀው ነበር። ሀሳቤ ከእሳቸው ራቀ የህይወት መንገድ ስለ ሞት መድሀኒት/ ዕጸ-ህይወት/ ከሞት ማምለጫ መሰወሪያ መጽሐፍ ጸሀፊ እና መጽሐፉ የት ሊኖር እንደሚችል እያሰብሁ ሳለ...

"መጣሁ እስኪ ልጄ" ብለው ከመቀመጫቸው ተነስተው ወደ መኖሪያ ጎጇቸው ገቡ። ትንሽ ቆይተው መጽሐፉን አስቀምጠው ተመለሱና...

"በቃ ልጄ ነገ ከነገ ወዲያ ተመልሰህ ና...." አሉኝ። መልሴ እሽ ነበር።

"መልካም አባ" አልኳቸው።

"በል ተነስ መሄድ አለብህ እኔም ወደ አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ገዳም መሄድ አለብኝ። ፈጣሪ ይባርክህ ያሰብኸውን ያሳካልህ። አገልግሎትህን ይባርከው ልጄ" መረቁኝ። የእሳቸውን ብርታት እና ጥንካሬ ሳይ አሁንም የኔ ድካም አሳዘነኝ። ሌሊት ቤተ-ክርስቲያን

ለምስጋና ቁመው፣ ምሽት ላይ ልጆችን ሲያስተምሩ ቆይተው ከዛ በጸሎት ይቆያሉ። ሌሊቱን ሙሉ እንዲህ አድረው ቀን በአንድ አንድ ስራዎች ሲባትሉ ይውላሉ። አሁን ደግሞ እርቀት ወዳለው ገዳም ሊያቀኑ ነው። ምርቃታቸውን በደስታ ተቀበልሁ። ተባርኬ ከተቀመጥሁበት ተነሳሁ። እሳቸውም ለመሄድ ጉዞ ሊጀምሩ እያሰቡ ነው። በምን እና እንዴት እንደሚሄዱ አሁንም ድረስ አላውቅም። ምናልባት እንደ ነብያት እና ሀዋርያት በደመና? ገዳሙ ደግሞ እንደሰማሁት አይደለም እንኳን በሽማግሌ እግር ቀርቶ በእኛ በወጣቶች ከስድስት ሰዓት በላይ ይወስዳል ይባላል።

"አባ ምናልባት ሰዓቱን እረሱት ሰዓቱ ሂዱል እኮ" አልኋቸው። እሳቸውም በትናንሽ ዓይኖቻቸው አተኩረው እየተመለከቱኝ።

"ግድ የለም ልጄ ግድ የለም አንተ ከፈለግህ እዚሁ ማረፍ እና መቆየት ትችላለህ። ከፈለግኸኝ ነገ ጠዋት በኪዳን ሰዓት እንደምንገናኝ እምነቴ ነው። በቃ ደህና እደር" አሉኝ። እንደገና ወደ ቤታቸው ገቡና ቀድሜ የሰጠኋቸውን መጽሐፍ ይዘው በመውጣት የቤታቸውን በር ዘግተው ቁልቁል በውስጥ ለውስጥ መውጫቸው ጉዞ ጀመሩ።

በዚህ መንገድ ከአባ እና ከአንዳንድ ታላላቅ አባቶች በስተቀር ማንም ሰው መሄድ አይችልም። የሚሄዱበት የአቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ገዳምም የሚታወቀው በቅዱሳን አባቶች ብቻ ነው። ዳር እና ዳሩ በሾህ ተክል የተከበበ መሀሉ ደግሞ ለእግረኛ ብቻ የተከፈተ የእግር መንገድ እንደሆነ ሰሰማ ብኖርም ከቅዱሳን አባቶች በስተቀረ ማንም ሰው ሄዶበት አያውቅም። ጎንደር አባ እና እኔ ከመጣን በኋላ በሰማሁት ጥንት በሚባል ድሮ ውስጥ ከቅዱሳን ውጭ በዚህ መንገድ ለመሄድ የሞከረ ሰው ለሞት የሚያበቃ በሽታ ላይ እንደሚወድቅ ሰምቼ አምኛለሁ። የዚህ መንገድ መጀመሪያው እንጅ መጨረሻው የት እንደሆነ የሄዱበት ብቻ ናቸው የሚያውቁት።

አባ ባህሪ በሄዱበት በዚህ መንገድ ለመሄድ እና ስለዚህ መንገድ መዳረሻ ሁሉን ለማወቅ የሚፈልጉ አንዳንድ ደፋር የቆሎ ተማሪዎች ትዝ አሉኝ:: ለመሄድ በማሰባቸው ከባድ ቅጣት እንደተከናነቡ እና ስውነታቸው ላይ ቁስል እንደወጣ የታሪክ ምስክር ነኝ:: መንገዱን ስመለከት ቆየሁና ከተቀመጥሁበት ተነስቼ አባ የት እንደደረሱ ሳይገባኝ ከግቢው ለመውጣት ጉዞየን ጀመርሁ:: የደረሱበትን ቦታ ለማወቅ ብፈልግስ በምን አውቃለሁ:: አባ ባህሪ ከአይኔ ከተሰዎሩ በዙ ደቂቃዎች አልፈዋል:: አይኔን መለስሁ በግቢው የተለያዩ ቤቶች መኸሳትን ተመለከትሁ:: አትክልት የማጠጣት እና ሌሎች ስራዎች እየሰሩ ነበር::

የግቢውን በር የእንጨት መዝጊያ ከግቢ ወጣሁና እጄን በቀዳዳ አሾልኬ በውስጥ በኩል ቀረቀርሁት:: ትንሽ ራመድ ብዬ ተማሪዎች ከሚኖሩበት ግቢ ደረስሁ:: ከተማሪዎች አቅራቢያ የሆነች ጥግ ፈልጌ ከአንድ የግንብ መቃብር ላይ ተቀመጥሁ:: ተማሪዎቹ እየተከታተሉኝ ነበር:: ከኪሴ የተወሰነ ገንዘብ አወጣሁና...

"ልጆች ስንት ናችሁ?" ጠየቅኋቸው

ሁሉም አይናቸውን ወደ እኔ ጣሉ

"ሃያ" አለ አንድ ወፍራም እና ረጅም የቆሎ ተማሪ በርቀት ተቀምጠ ጓደኞቹ የሚሰሩትን ሁሉ በትኩረት እያስተዋለ ያለ ይመስላል:: ሌሎች በዝማሬ፣ በጸሎት አንዳንዶች ደግሞ የለመኑትን ደረቅ እንጀራ እያገላበጡ በስራ ተጠምደው ያሉ ቢሆንም እሱ ግን ወይ በስንፍናው አልያም አዲስ የቆሎ ተማሪ ስለሆነ ተመልካች ነው::

"ጥሩ ና አንተኛው በዚያውም የሚበላ ከደረቀው እንጀራ አምጣልኝ" አልሁት:: ወጣቱ እና ግዙፍ የቆሎ ተማሪ እንዳልሁት በፀሀይ እየሞቀ ከተሰጣው የደረቀ እንጀራ የተፈረፈረውን አፍሶ በሰፊ ቅጠል አድርጎ ይዞልኝ መጣ:: አመስግኜ ተቀበልሁና እኔም ለሃያው



ተማሪ የሚሆን እንዲካፈሉት አሳስቤ መቶ ብር ከኪሴ አውጥቼ ሰጠሁት:: ይሄ ብር ተማሪን አያባልግም ቢበዛ ለሾህ ማውጫ የአንድ መርፌ ቁልፍ እና የልብስ መጠቆሚያ የሚሆን መርፌና ክር ቢገዛ ነው:: እነሱም ከዚህ ውጭ ብሩን አይጠቀሙበትም:: የእነሱ ምግብም ሆነ ልብሳቸው በአብዛኛው የሰው ነው::

ተማሪዎቹ ደስ አላቸው:: እኔም ደስ አለኝ ከቅጠሉ ያለውን የተፈረፈረ ደቃቅ ደረቅ እንጆራ ወደ አፌ በመክተት ማብላት ጀመርሁ:: ከምግቡ ጋር አፈር አብሬ ስበላ ተሰማኝ:: ጥርሴ ከጠጠሩ ጋር ተፋጨ ደስ የማይል ስሜት ነበር:: ሩቅ በሀሳብ ፈረስ ተጓዝሁ የያኔ የድሮ ዘመን ትዝታዬ ታውሰኝ...

ሠይሠት

ትዝታ

ደግሰው በክርስትና ስሜ ወልደ ሚካኤል እባላለሁ። የተወለድሁት ጎንደር ጎንደር ዙሪያ ወረዳ በሚገኝ ጺዮን ሰጓጅ ቀበሌ ማህበር ውስጥ ነው። አባቴ በዛው አካባቢ በባላአባትነት ከሚጠሩት ሰዎች የተወለደ ሲሆን ስሙም አቶ ዳመናው አረጋ ይባላል። እናቴ ደግሞ ከትግራይ ግዛት የመጣች በአካባቢው የታወቀ ስም የሌላት ሴት ነበረች። ስሟ ደግሞ ለተ-ሰንበት ኪዳኔ ይባላል። በዚህ ከተማ ባለች የገጠር ቀበሌ ማህበር ሻይ፣ አረቄ እና ሌሎች ነገሮችን በመሸጥ የምትተዳደር ሴት ስትሆን ከአባቴ ጋር የተገናኙትም በንግድ ቤቷ ነው። ፍቅር ሁለቱንም አገናኛቸው እና በአንድ ገመድ አስሮ ይጎትታቸው ገባ። አባቴ በዘመኑ ከልጅነት እድሜው ጀምሮ ጀግና፣ ሰዎችን የሚያስተባብር፣ በማህበረሰቡ ዘንድ ተወዳጅ፣ መልከ መልካም የሚባል ሰው ሲሆን እሷም ይሄ ቀረሽ የማትባል ስለመሆኗ ይነገራል። ለመጀመሪያ ቀን ሲያያት... ልቡ ደነገጠ፣ ወደዳት በዚህም ምክንያት ወደ አረቄ እና ሻይ ቤቷ ይመላለስ ጀመር። ቀን ከቀን ሲገናኙ እርስ በእርስ ሲቀራረቡ አብሮ ስለመኖር ለመንደሩ አዲስ ሆና በመጣችበት ወቅት አወሩ። የፍቅርን ቤት ተጋሩ... ይሄ ግን የአባቴ ባለአባት ዘመዶቹ ዘንድ ሊወደድለት አልቻለም። ኮማሪት፣ አረቄና ሻይ ሻጭ ሴት እንዴት ታገባለህ በሚል ፊታቸውን አዞሩበት።

እሱ ግን የእነሱን ተግሳፅ እና ቁጣ ችላ ብሎ እሷን አግብቶ ከቤተሰቡ በመራቅ ወደ እዚህ ጎንደር ከተማው ውስጥ በዙሪያው ወዳለች መንደር ይዟት መጣ። በዚህም የተነሳ ከቤተሰቡ ጋር የነበረው የግንኙነት ሰንሰለት ለመጨረሻ ጊዜ ተበጠሰ።



አዲሱ መንደራችን በመጣንበት ዓመት ብዙ ችግር ቢደርስበትም ከዓመታት በኋላ እየቆዬ ተስተካከለ:: አባት እና እናቴ በመካከላቸው ያለው ፍቅር ሰዎችን ቢያስቀናም ልጅ ግን በፈለጉበት ሰዓት ፈጣሪ ሊሰጣቸው አልቻለም:: በዚህ የተነሳ በየቤተ ክርስቲያኑ እየዞሩ ስዕለት ሲሳሉ ኖረው በስተመጨረሻ እኔን ወለዱ:: ቤቱም እንደሚባለው በኔ መወለድ የተነሳ የበረከት ቤት ሆነ:: ከእኔ ጋር ሀብት እና ክብር ወደ ቤት ገባ:: አባቴ በጥቂት ዓመታት ውስጥ በጣም ሀብታም እና ተሰሚነቱ እየጨመረ መጣ:: ለተቸገሩት አዛኝ፣ የአካባቢውን ሰው የሚያስተባብር፣ ለሚኖርበት መንደር እድገት ተቆርቋሪ፣ በሽምግልናውም በደስታ እና በሀዘኑም በግንባር ቀደምትነት የሚገኝ ሰው ሆነ:: እኔ በተወለድሁ በአራት ዓመቴ ግን ከአስራ አምስት አመት በላይ ከጎኑ የነበረች እናቴ ለተ ሰንበት ኪዳኔ የእናትነት ፍቅሯን ሳልጠግበው በብርድ ምክናያት በተነሳ በሽታ ሞተች::

እኔ በጊዜው ልጅ በመሆኔ ባልረዳ እና ባላውቀውም አባቴ ለሁለት ዓመታት እንዳዘነ ሰምቻለሁ:: ከጎኑ ያሉ ሰዎች ቢያፅናኑትም ሊሰማ አልቻለም:: ለኔ ወንድም ወይም እህት ባለመኖሩ ይባሱኑ ከፋው:: ምናልባት እናቴ በመሞቷ የተነሳ ምክንያቱ አባቴ እና እናቴ ስለረገሙት እንደሆነ ማሰብ ጀምሮ ነበር:: እየቆየ ዓመታት ሲሄዱ ሰው ሞተ ተብሎ ነገን ማየት መዋሉ እና ማደሩ አይቀርምና እንደገና ተስፋው እየለመለመ ሀዘኑ እየጨለመ እየመነመነ እየሄደ የሀዘን ፊት እና ልብሱን አውልቆ ወደ አዲስ ህይዎት ሊያመራ ይዘጋጅ ጀመር::

አንድ ዓመት አለፈ በዛ ዓመት ግን በሰሜን ግንባር የደርግን ጦር አሸንፎ ህ.ወ.ሓ.ት ከሌሎች አጋሮቹ ጋር በመሆን ወደ ጎንደር ከተሞች እየገባ ነበር:: ሁሉም ሰው ካለፈው መንግስት የተሻለ ኑሮ እንኖራለን በሚል ህ.ወ.ሓ.ትን ከመውጋት ይልቅ አብሮ እየተመመ ደርግን መውጋት እንዲሁም ለህ.ወ.ሓ.ት እና ለደጋፊዎቹ ጦር ስንቅ እየሰጠ እነሱን ሲያበረታታ ነበር:: አባቴ በፖለቲካው ሳይሳተፍ ከውጭ ሆኖ

ይሄን ሲመለከት ቆዬ:: የእኔ እድሜ ያኔ ሰባት ዓመት ነበር:: አባቴ የሞተውም በዚያው ዓመት ህዝብ በተቀበላቸው የህ.ወ.ኃ.ት. ጦር አባሎች ነው:: ያ ዓመት ጀሮዬን ይዤ የአስኳላ ትምህርት ቤት የገባሁበት ዓመት ነበር:: በወላጅ አባቴ መሪነት የቄስ ትምህርት ከገባሁ ስለቆየሁ የተሻለ ስለ ትምህርት አውቃለሁ:: ብዙም ሳይቆይ ጦርነቱ ተጠናቀቀ እና በሀገሪቱ የመንግስት ለውጥ ተካሄደ:: በወቅቱ ህዝቡ ግራ የተጋባ ይመስላል:: ደርግን በመሸኘት ኢ.ህ.አ.ዴ ግን በመልካም ቢቀበልም ነገሮችን እንዳሰባቸው ሆነው አላገኛቸውም:: አማራ እራሱን በራሱ እንዲያስተዳድር ነጻነቱ እንዲከበር በተለይ ጎንደር አካባቢ እንዲጠናከር የማይፈልገው አዲሱ ህ.ወ.ኃ.ት በበላይነት የሚመራው የኢ.ህ.አ.ዴ.ግ. መንግስት በየመንደሩ ያሉ ቁልፍ ቁልፍ የሆኑ ሰዎችን አማራ ብቻ በመሆናቸው እያሳደደ እራሱ ለሚፈልጋቸው ታዛዥ እና ሆዳም ተላላኪ ሰዎች ስልጣን እየሰጠ ጠንካሮችን ደግሞ እንዳያስቸግሩት በማሰብ እየመረጠ የሸፍታ፣ የገዳይ ስም እየሰጠ የመግደል ስራ ላይ ተጠመደ:: የአማራ አካባቢዎች ተቆርቋሪ ነን የሚሉ ሰዎችን በየቦታው ባሉበት ታድነው ይገደሉ፣ ይሳደዱ፣ ይንቋሸሹም ጀመር::

ምናልባት ሰው አይኑን በቀደመው ጨቋኙ እና ገዳዩ የደርግ መንግስት ተወግዶ ማየቱ ላይ አድርጎ የእኔን አባት እንባ ሊያይ አልቻለም:: ህዝቡ አንድ ሽፍታ ተባሮ ንፁህንን በራሱ ስም ሽፍታ እና ገዳይ እያለ የሚጠራ ዘር እና ማንነትን እየለየ የሚገድል... ሌላ ሽፍታ እንደሚመጣ አላስተዋለም:: አባቴ እና ለአማራ፣ ለአካባቢያቸው የሚቆረቆሩ አንዳንድ ከፊት የቀደሙ ሰዎች በደርግ፣ በኢ.ህ.አ.ዴ.ግ ጊዜም እየታደኑ ሞተዋል:: አባቴ እና ጓደኞቹ ለህዝብ፣ ለሀገራቸው፣ ለኢትዮጵያ ሲሉ እንጅ ለስልጣን አልነበረም የፈጁት: : ከፊት የቆሙት፣ ደርግን ሲፋለሙ ቆይተው ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ በቦታው ሲተካ በየቀበሌው በፖለቲከኝነት ያልተሳተፉትን ጨምሮ ተቆርቋሪዎችን እያደነ እየገደለ አዲሱን አሰራሩን እና አመራሮቹን

ሲተካ ያልተመቻቸው አባቴ እና ጓደኞቹ... ለምን? የሚል ጥያቄ ለማንሳት ተገደዱ::

"ለምን ይሄ ህዝብ ያለፈው በደል አይበቃውም?" ብለው ስልጣን ላይ ካለው መንግስት ጋር ግብግብ ገጠሙ:: ይሄ መሆኑን ያልፈለገው መንግስት ተደፈርሁ በሚል በሌሎች በታዎች እንዳደረገው እኛም ከተማ ውስጥ ሽፍቶች፣ ህዝብ ገዳዮች፣ በደለኞች በማለት ወንጅሎ በየቦታው ይለቅማቸው እና ይገድል ጀመር:: የኔ አባትም ከእነሱ አንዱ ሆነ:: ሰው የሰማውን እና የተነገረውን እያመነ ለሱ የተጋደሉትን እና የለፉለትን በፍርሀት እና በጥርጣሬ ተሸብቦ አብሮ ይወገዱ፣ ይገደሉ እያለ ያሳድዳቸው ጀመር:: ከዚህም አልፎ መንግስት የማያውቁትን እና ከአይኑ የተሰወሩትን ሽፍቶች እንዳሳወቃቸው ቆጠሩት:: ከዛም በህዝብ ፊት አደባባይ ላይ በጥይት ተደብድበው እንዲገደሉ ተደረገ:: ያን ቀን ይሄን ቁሜ ነበር በአይኔ የተመለከትሁት:: አባቴን አደባባይ ላይ አውጥተው በጥይት ደብድበው ገደሉት:: በአባቴ ሞት ፊቴ በእንባ ታጠበ፣ ጮኹ ወደ እሬሳው ሩጬ ሄጄ ከሬሳው አጠገብ ብቻዬን ተቀምጬ ያለ ጥፋቱ አጠፋ ተብሎ በጥይት ተደብድቦ በህዝብ ፊት የተገደለውን የአባቴን በድን ይዤ አነባሁ:: ሰው ለራሱ ጥቅም አባቴ እንዳልሞተ ሁሉ አላዘነልኝም:: ያስገደሉትም የአካባቢው ተወላጅ የሆኑ አዳዲሶቹ ባለ ስልጣኖች ነበሩ:: በቀጣይ የዚህችን ሀገር ንጹህን ሰዎች ደም የሚመልሰው ፈጣሪ ሆነ ዝም... ሁሉም ያልፋል ሰው ግን እንደ ቦይ ነው:: ጊዜ ጽድቁን እስኪያሳይ በከፈቱለት ይጓዛል::

ገዳይ ወታደሮች የአዛዦቻቸው የደም ጥማት ሲረካ ሬሳውን መንገድ ላይ ጥለው ወደ ሚሄዱበት ሄዱ:: እኔ ግን ከሬሳው አጠገብ ነኝ:: ብዛት ባለው ጥይት የተበሳሳው የአባቴን አስከሬን ይዤ አየጮሁ ነበር:: ከሰውነቱ የሚፈሰውን ደም ለመሸፈን እታገላለሁ:: ሳዉ ይሄን ትዕይንት እንደ ሲኒማ ተከታትሎ ወደ ቤቱ ተመለሰ::

ብቻዬን ነበርሁ። ከደቂቃዎች በኋላ አንድ ሰው ከአጠገቤ መጥቶ ልብሴን እየጎተተ ሲያለቅስ ሰማሁ። ደነገጥሁ 'ማን ነው?' ያ የሚጎትተኝን ሰው ዞሬ ለመመልከት ሞከርሁ። አይኔን በእንባ አርሼ ወደ መጣው ሰው ዞርሁ። በእኔ እድሜ ላይ ያለች ህፃን ልጅ ነበረች። እሷም እያለቀሰች ከአይኖቿ እንባ እየፈሰሰ ተመለከትኋት። እንደ እኔ የተጎዳች ትመስላለች። ልብሴን እየጎተተች እንድነሳ ለማድረግ ትጥር ነበር። ያለሁት በዚህ አባቴ እና ሌሎች የማላውቃቸው ሰዎች ሽፍታ፣ ገዳይ፣ ሌባ፣ የደርግ ተላላኪ ተብለው በተረሸኑበት አደባባይ ላይ ነው። ምናልባት አባቷ እንደ እኔ አባት በግፍ ሞቶ ይሆን? በአስተዋልኋት ቁጥር ግን ልጅቱ ከዚህ አደባባይ በቅርብ እርቀት ከእኛ ቤት አጠገብ ያለች በእድሜ የእኔ እኩያ ስትሆን ስሟ ማንአህሎሽ ይባላል። ልብሴን ይዛ ትጎትተኛለች። ሁሉም ሰው ወደ ሰራው ቤቱ ገብቶ በቦታው ሳይኖር እርሷ ብቻ ለእኔ አዘነችልኝ። እኔን እየጎተተች እና እያለቀሰች እኔም እያነባሁ ደቂቃዎች አለፉ። ቆይቶ ግን አባቷ መጥቶ ልጁን ከእኔ አጠገብ ሊወስድ ሞከረ። እሷ ግን ቢጎትታትም ልብሴን ይዛ ልትለቀኝ አልቻለችም። ለምን እንደሆነ አላወቅሁም? አዋቂዎች ምንም ባይሉም እሷ ግን ህሊናዋ እንቢ አላት። ጥላኝ ላለመሄድ የወሰነች ትመስላለች።

የማን አህሎሽ አባት የልጁ ለቅሶ እና የእኔ ሀዘን ወደ ልቡ መለሰው መሰለኝ ወደ ልጁ እየተመለከተ እኔን እያየ...

"ና ልጄ አንተም መሄድ አለብህ ወታደሮች ተመልሰው ይመጣሉ። አንተንም ይገሉሀል ተነስ ተነስ..." ብሎ ማንም እንደሌለኝ ስለሚያውቅ አስገድዶ ከሬሳው ላይ አንስቶ ወሰደኝ። ከአካባቢው እየጎተተኝ ልጁም ጨርቄን ይዛ አብረን ወደ ቤታቸው ተጓዝን። ትንሽ እንደራቅን ግን ሬሳ ጫኝ መኪኖች ከወታደሮች ጋር መጥተው የአባቴን እና የሌሎች ሰዎችን አሬሳ ጭነው ሄዱ። ከዓመታት በኋላ ወዳወቅሁት መቃብር ቦታ ወስደው ቀበሯቸው። በየዕለቱ ብዙዎች

ቢሞቱም ትውልድን የሰው ልጅ ማጥፋት አይችልምና በሄዱት ልክ አዲሱ እየተተካ የሄዱት ተረስተው አዲሱ ሰው ትግሉን ይቀጥላል::

***

ከነ ማንአህሎሽ ቤት በእሷ የተነሳ ገባሁ:: አብሬያቸው መኖር ጀመርሁ:: የማንአህሎሽ አባትም ሆኑ እናቷ ስለዚያ አባቴ ስለሞተበት ቀን ሲያነሱ ዛሬም ድረስ ይገረማሉ:: አዲሶቹ የኢትዮጵያ አስተዳዳሪዎች ሁሉንም አሳጡኝ:: ግን መልካም ሰዎችን ደግሞ ፈጣሪ ሰጥቶኝ እነሱ አስጠጉኝ:: ሁሉም ነገር ለበጎ ነው የሚባለው ለዚህ አይደል:: ሁሌም በቤቱ ስለዚያ ቀን ሲወራ

"በነፍስ የደረሰችለት ብቸኛ እንዳይሆን የረዳችው ያየችው እና ያዘነችለት ማንአህሎሽ ብቻ ነበረች" ይላሉ:: ለዚህ ደግሞ የእሷ ቤተሰብ ብቻ ሳይሆን አባቴ በግፍ ሲገደል እንዳላዬ ያለፈው የአካባቢው ማህበረሰብ ምስክር ነው:: እኔም ቢሆን የእርሷን ውለታ አልረሳውም:: ለዚህ መድረሴ ለህይወቴ መስተካከልና ማማር ምክንያቷ እርሷው ነች::

ቀናት ሲገፉ የማን አህሎሽ አባት እንደ ልጃቸው ተቀበሉኝ:: ከስሜ በግፍ የተገደለ አባቴን ስም ባይፍቁም አባቴ ሆኑ:: እናቷም ቢሆን እንደዛው አደረጉ:: ልጃቸው ስብሀት የአስኳላ ትምህርት መግቢያው ጊዜ ደርሶ ሁለታችንንም በአንድ አይነት እድሜ እርከን ላይ ስለነበርን የአስኳላም፣ የቄስ ትምህርትም እንድንማር በማሰብ እዛው አካባቢ በሚገኝ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት አስገብተው ሌላውን ትርፉን ጊዜዬ ደግሞ የቄስ ትምህርት እዛው እየኖርን እንድንቀጥል አባ ባህሪ ለሚባሉ አባት በአደራነት ሰጡን:: ከዚህ ጊዜ በኋላ ለዓመት በዓል ወይም ክረምት ለስራ በምንፈለግበት እና የእረፍት ጊዜ ካልሆነ ውሎ አዳራችን ቤተ-ክርስቲያን ውስጥ ሆነ...

በዚህ ጊዜ ማንአህሎሽ ከወንድሟ ከአጠገቧ መራቅ ይልቅ የእኔ ከቤት መራቅ ነበር ያሳሰባት:: የስብሀት አባት እና እናትም ቢሆኑ

ከስብሀት በላይ በማን አህሎሽ መወደዱ ያስገርማቸው ነበር። ይሄ ሰዋዊ ሳይሆን የአምላክ ስራ ነበር የሚመስለው። ደግሞም ነው የእሷ አንበና ለቅሶ ጎዳና ላይ ከመውደቅ አድኖኛል።

የማንአህሎሽ አባት እና እናት የሚተዳደሩት ባሉበት መንደር በእጅ ስራ ሙያ ሲሆን አባት የአካባቢውን ሰዎች ልብስ በመሸመን እናቷ ደግሞ የሸክላ ዕቃዎችን በመስራት ነው። በወቅቱ በአካባቢው ማህበረሰብ አባል ገበሬዎች፣ ነጋዴዎች፣ የቆዳ ሰራተኞች፣ ዝቅተኛ አየተባሉ የሚገለሉና የሚንቋሸሹ ቢሆንም ከሁሉም በላቀ ሁኔታ ግን አንደነሱ አይነት ሰዎች የተገለሉ ናቸው። እነሱን ለጋብቻ፣ ለዝምድና፣ ለጉርብትና እና ለጓደኝነት የሚቀርብ የሚጠይቅም ሰው አልነበረም፡ ፡አራሹ አፈር ገፊ፣ ቆዳ የሚያለፋው ፋቂ፣ ነጋዴው መጫኛ ነካሽ፣ ሸማ ሰሪው ሸማኔ፣ ብረት ሰሪው ቀጥቃጭ .... ሌላው ሌላ እየተባለ በማህበረሰቡ ውስጥ አንዱ ከአንዱ መለያ ሰም እየተሰጠው እና እየተለየ ይኖር ነበር። በቆየው ጊዜ የአንዱ አጥንት ከአንዱ የጎደለ ይመስል፣ የአንዱ ዘር ከአንዱ እንደሚያንስ ሰዎች ተፈጥሮ የሰጠቻቸውን አንድነት ትተው እራሳቸው ባዘጋጁት የስራ መስፈርት ዘር እየተቆጠሩ የኋላ ቤተሰብ እየተማዘዙ እርስ በርስ አንዳቸው ከአንዳቸው ይገለሉ ነበር። እየቆየ ድሀ፣ ሀብታም ሰው ገንዘብ ካለው፣ ከሌለው መለየት ጀመረ። አሁን ደግሞ አማራ፣ ኦሮሞ፣ ትግሬ፣ ጉራጌ፣ ሱማሌ፣ አፋር እየተባለ ዘር ለዘር በሌላ መስፈርት ይለያይ ጀምሯል። መንግስታት ሀገርን ለዘመናት ለመግዛት እና በቁጥጥራቸው አርገው ህዝብን ለመርገጥ ሲፈልጉ አንዱን ከአንዱ ማጣላት እርስ በርስ ማጋጨት አለባቸውና ይሄን ህዝቡ ሳያውቀው ወይ ለመረዳት ሳይፈልግ እስከ አሁንም አለ...

የማን አህሎሽ እናት ከሁሉም በተለየ በአካባቢው ሰለሚባለው ከር ግድ አይሰጣቸውም። የኔ አባት የባላባቶች ዘር እንደሆነ በሰሚ ሰሚ ቢያውቁም



"ኧረዲያ ምን አገባን ሰው የሚለው... የሚያሞረን ሰራችን ነው። ሰው ያሻውን ይበል ሌላም ቢሆን ማለቱ አይቀር ሰው የሚለውን አያጣ" ይላሉ። የማንአህሎሽ አባቷ ከልብስ መስፋት በተጨማሪ እዛው አካባቢ በሚገኘው እኛ በምንማርበት ቤተ-ክርስቲያን በቄስነት ያገለግሉ ነበር። ለዛም ነው ልጃቸው ሰብሀት እና እኔን በመደበኛ ትምህርት ብቻ ሳይሆን በቄስ ትምህርት የተሻሉ ልጆች እንድንሆን ለአባ ባህሪ የሰጡን። ማን አህሎሽንም ቢሆን ከእኛ ሁለት ዓመት አዘግይተው ወደ አስኳላ ትምህርት ልከዋት ነበር።

***

የእኔ እና የሰብሀት የቄስና የአስኳላ ትምህርታችን በጥሩ ሁኔታ ቀጥሎ ነበር። የቄስ ትምህርት መማራችን ለዓለማዊ ትምህርታችን መሰረት ሆነና በዓለማዊ ትምህርታችን አንደኛ እና ሁለተኛ ደረጃ ይዘን በፉክክር እንወጣ ጀመር። ቀስ በቀስም እያደግን ስንመጣ የቄስ ትምህርት ቤቱን ስንለምድ አዲስ ወደ ቄስ ትምህርት ቤት የሚመጡ ተማሪዎችን እየተቀበልን የማልመድ ስራ እንሰራ፣ አባ ባህሪ በሚደክሙበት እና አንዳንዴ ለተለያዩ ጉዳዮች ከአካባቢው እርቀው በሚሄዱበት ሰዓት ፈደል፣ ንባብ እንዲሁም የሀይማኖት ትምህርቶችን የምናስተምር የአባ ባህሪ ቀኝ እጅ፣ ታማኝ፣ ቅን እና ታዛዥ ልጆች ሆነን አረፍን። በአካባቢው ሰውም መልካም የቆሎ ተማሪዎች መሆናችን ይመሰክር ጀመር። መልዕክተ ዩሐንስ፣ ውዳሴ ማሪያም፣ አንቀጸ ብርሃን፣ መልከዐ ማሪያም፣መልከዐ ኢየሱስ፣ መዝሙረ ዳዊት እና ሌሎችን ተማርን። ዲቁናችንንም ያዝን። ስንቀድስ ድምጻችን የማይጠገብ፣ የሀይማኖት ትምህርት የዘለቀን፣ እንዲሁም ክርስቲያናዊ ስነ-ምግባር ያለን ተማሪዎች ነበርን።

የአስኳላ ትምህርታችን ከፍ እያለ ኢድሜያችን እየጨመረ ስምንተኛ ክፍል መልቀቂያ ፈተና ወስደን ዘጠነኛ ክፍል ደረስን። በዚህ ጊዜ ነበር ከአባቢው መራቅ እና ጎንደር ከተማው መማር

ለንዳለብን ያወቅነው:: በወቅቱ ከዘጠነኛ ከፍል ጀምሮ የሚያስተምር ትምህርት ቤት በአካባቢያችን አልነበረም:: ተከራይተን ብቻችንን ሆነን ለመኖር ደግሞ ገንዘብ ያስፈልግ ነበር:: በዚህ የተነሳ ግራ በመጋባት ስሜት ተዋጥን:: እኛን የአስኳላ ትምህርት ለማስተማር የማን አህሎሽ አባት እና እናት የማይችሉበት ጊዜ ላይ ደረሱ:: በዚህም ልጃቸው ስብሀት እዛው የእነሱን ስራ እየሰራ ቄስ ሁኖ ቤተ-ክርስቲያንን እንዲያገለግል እኔንም እንደዛ እንዳደርግ አዘዙን:: ስብሀት ተስማማ እኔ ግን በእነሱ ሀሳብ አልተስማማሁም::

የአስኳላ ትምህርቴን መቀጠል እንዳለብኝ ወሰንሁ:: ለስብሀትም ቢሆን ምክሬ ይሄ ነበር:: እሽ አላለኝም... አባቴ ከሞተ በኋላ ሰዎች ተጠምደውት እያረሱት ያለው መሬት ሸጠው እኔ እና ስብሀት እንዲያስተምሩን ተናገርሁ:: የእሱ ቤተሰቦች እና እሱ በእኔ ሀሳብ አልተስማሙም:: ለዚህ ተብሎ የአባቴ መሬት እንደማይሸጥ ተነገረኝ::

በምሄድበት የሚገጥመኝ ሁሉ ገጥሞኝ መማር ስለፈለግሁ አስረድቼ ፍቃድ ተሰጠኝ:: ወደ ጎንደር ከተማው ለመሄድ ዝግጅቴ ተጀመረ:: ወደ ከተማ ሄጄ የምኖረው ለመጀመሪያ ጊዜ ነው:: ለዚህም ቀደም ተብሎ ለሁለት ወራት የሚሆነኝ፣ የሚያስፈልገኝ እህል እና ገንዘብ ተዘጋጀልኝ::

***

ጎንደር በገባሁ በመጀመሪያው በዚያኑ ቀን አንድ ክፍል ቤት ተከራየሁ:: በዚያው ቀን ማታ ላይ እዛው ከገዛሁት የሳር ፍራሽ ላይ ተቀምጬ ከቤት ያመጣሁትን ጓዜን በመክፈት በተከራየኋት አነስተኛ ክፍል በትኜ፣ እርቦኝ ስለነበር ነገ ከነገ ወዲያ ማብሰያ እቃዎችን እስከገዛ እንጀራ ገዝቼ ስለነበር ሽሮ ፈትፍቼ ልበላ ስላሰብሁከቤት ያመጣሁትን በትንሽ ማዳበሪያ የተቋጠረ ሽሮ ከፈትሁት:: ላዩ ላይ አንድ በአራት መዓዘን የተጻጸፈ ወረቀት በሽሮ ተቀባብቶ አየሁ:: ምን

ይሆን? ማን እዚህ ውስጥ እንዳደረገው አላውቅም ገለጻውን
የተጻፈበት ነበር። ማንበብ ጀመርሁ....

"ሰላም ደግሰው ምን እንደሆነ አላውቅም ግራ በመጋባት ውስጥ
ነው ያለሁት። አንተ ምናልባት ይሄን ላታምነኝና ላትረዳኝ ትችላለህ
እኔ ግን ካለ አንተ መኖር አልችልም እጅግ በጣም አፈቅርሀለሁ።
እህቴ ነሽም ልትለኝ ትችል ይሆናል እኔ ግን አልችልም አንተ
አብረኸኝ ካልሆንህ እሞታለሁ። እባክህ እባክህ እባክህ እሞታለሁ
ይሄን ጊዜው አይደለም ብለ እንጅ እማም ታውቃለች። ማንአህሎሾ
ይላል ደነገጥሁ ስትጽፈው አይኔን እየየች የምታወራ ይመስላል። ማን
አህሎሸን እንደ እህት እና አዳኜ ነበር የማያት ዛሬ ግን እንደ
ምታፈቅረኝ እየነገረችኝ ነው። ይሄን እናታችንም ታውቃለች።

ማን አህሎሸ ካላፈቀርኋት አብሬያት ካልኖርሁ እሞታለሁ
እያለች ነው። የህይወቴ አዳኝ እሷ ነበረች። ግራ ተጋባሁ አዳኜን እኔ
ልገላት አልችልም። ማን አህሎሸን እወዳታለሁ እንደ ፍቅረኛ እንደ
ሚስት ግን ደብዳቤውን ካነበብሁ በኋላ ነው ያሰብሁት። ነገሩ
አልከፋኝም ስለ ፍቅር እንዳስብ ሆንሁ... ሁሉ ሀሳቤ በነዚያ
ባሳለፍናቸው አብረን በኖርንባቸው ዘመኖች ላይ ሆነ አብረን
አድገናል እንደ ፍቅረኛ ቢከብድም ስለዚህ ጉዳዩ እናቷ ታውቃለች
"የቆየ መሆን አለበት" እላለሁ ለራሴ... እንዴት ወደ ፍቅር እንደገባች
ባላውቅም እንደምታፈቅረኝ ስለነገረችኝ ደስ ብሎኛል። እሷም ይሄን
በቋጠረችው ጓዝ ስለነገረችኝ ደስ ብሏት እርፍ ብላ ይሆናል። ምሳ
ሰርቼ መብላቱን በመተው ስለ እሷ ብቻ አሰብ ጀመር።

***

ከነበርሁበት የገጠር መንደር ወደ ጎንደር ከተማ ከገባሁ ቆየሁ።
ሆኖም አሁንም ከቤተ-ክርስቲያን አልራቅሁም። ጎንደር ከተማ
ቀድሞ በፋሲል ዘመን እንደ ሀገረ መንግስቱ መናገሻ ሆና ያገለገለች
ሲሆን ብዙ ነገስታት ስልጣን ላይ ወጥተው የወረዱባት፣አፄ ፋሲል

በ1636 ዓ.ም ያሳነጹት ግዙፍ ህንጻ ጨምሮ ሌሎች ታሪካዊ ሁነቶችን ይዛ ለሀገር አንድነት የታገሉትን አፄ ቴድሮስን እያነሳች እና እየዘከረች የምትኖር ከተማ ነች። በወቅቱ በከተማዋ ዘመናዊነት እየተስፋፋ ቢሆንም ዛሬም የጥንት ከተማነቷን የሚዘክሩ አብያተ ክርስቲያናት የነገስታት እና መኳንንት ህንጻዎች እንዲሁም የልጆቿ ታሪኮች አሉ። ህዝቦቿም ዛሬም እንደ ጥንት ደግነት፣ ኩራት፣ ጀግንነት እና ሀገር ወዳድነትን እንደለበሱ ናቸው።

ሁሌም ትምህርቴን ተምሬ ስጨርስ የሰርክ ሰዓት ላይ እንዲሁም ቅዳሜ እና እሁድ ሁሌም ከቤተ-ክርስቲያን አልጠፋም። ከሶስት ወራት በኋላ አባ ባህሪ ወደ ጎንደር አሁን ወደ ሚያገለግሉበት ቤተ ክርስቲያን ተዘዋውረው መጡ። ይሄ ደግሞ ለኔ ሌላ ጥሩ አጋጣሚ ሆነ። በሰንበት ትምህርት ቤት እንዲሁም በየቅዳሴው እየተገኘሁ ፈጣሪን ማመስገን እና ማገልገል ጀመርሁ። በድምጼ፣ በዕርጋታዬ ከዛም አልፎ ያለችኝን ትንሽ እውቀት ለሰዎች ለማካፈል በመሞከሬ ሁሉ ሰው ይወደኝ ጀመር። ወደ ቤተ-ክርስቲያንም በደንብ እንድቀርብ ሆነ። ስብሀት አንዳንዴ ከገጠር እህል ይዞልኝ ወዳለሁበት ከተማ ይመጣል። እኔ ግን ብዙም ሳልቆይ በቤተ ክርስቲያን እና በትምህርት ገበታዬ የሚያውቁኝ ሰዎች ልጆችን እያስጠናሁ አብሬያቸው እንድኖር ሰዎች ቤት ገባሁ። አባ ባህሪ በአቅራቢያዬ በመኖራቸው ህይወቴም ቀስ እያለ ቀን ከቀን እየተስተካከለ መጣ።

***

ዘጠኝ፣ አስር፣ አስራ አንደኛ ክፍልን አልፌ የአስራ ሁለተኛ ክፍልን ፈተና ወስጄ ውጤት እየተጠባበቅሁ ነበር። ከዚህ ቀደም በየአመቱ ክረምት፣ ትምህርት ሲዘጋ ወደ መንደር ስሄድ አልፎ አልፎ እነሱ እኔን ለማየትም ሆነ ለሌላ ስራ እኔ ጋር ሲመጡ ማን አህሎሽን እና ቤተሰቤን ባገኝም ከማን አህሎሽ ጋር እየተያየን በመተፋፈር

ስሜት ውስጥ ሆነን በፍቅር መፈላለጋችንን ለጊዜውም ቢሆን በውስጣችን ችለን አብረን እንደ አህት እና ወንድም ብናሳልፍም በአሁኑ ዓመት ወደ መንደር በሄድሁበት ወቅት ማንአህሎሽ ከአራት ዓመት በፊት በቋጠረችልኝ አህል ውስጥ በደብዳቤ የጠየቀችኝን ከዚህ በኋላ ነግራኝ በመተንፈሷ የተነሳ ዝም ያለችኝን ጥያቄ ደግማ አነሳችልኝ:: እንደምታፈቅረኝ አብረን አንድንኖር እንደምትፈልግ የእኔን መልስም ጠየቀችኝ:: እኔም በሚገባ በሰጠችኝ አራት ዓመት ሳስብበት ስለነበረ፣ ቤተሰቦቿም ቢሆኑ ስለዚህ ስለሚያቁ ትምህርት ስጨርስ ሁሉም እንደሚሆን አብረን እንደምንኖር ከዚያ ቀን ጀምሮ ፍቅረኞች እንደምንባል ቃል ገባሁላት:: ስመረቅ እንደማገባት አብረን እንደምንሆን በቤተሰብ ፊት አወራን:: ሁላችንም ደስተኞች ነበርን...

***

አስራ ሁለተኛ ክፍልን ከፍተኛ ውጤት በማምጣት ጅማ ዩኒቨርስቲ የሳይኮሎጂ ትምህርት እንደደረሰኝ ካወቅሁ ቀናት ተቆጠሩና ወደ ጅማ ሂጄ ትምህርት እዛው መከታተል ጀመርሁ::

ጥንታዊቷ የአባ ጅፋር ከተማ ከ1950 ዎቹ በፊት የምዕራብና ደቡብ ኢትዮጵያ አንጋፋ ገበያ የበረች ሲሆን በውስጧም ብዙ የቀድሞ ነገስታት ከትመው ነበር:: በቡና ምርቷ፣ በልምላሜዋ የምትታወቀው የደግ ህዝቦች መኖሪያ ጅማ የህዝቦቿ፣ እና የነገስታቶቿ ታሪክ እና ዝና ታላቅ ቢሆንም እንደ አደግሁባት ጎንደር በዘመኗ ብዙት ልክ አላደገችም:: ጅማ በነበርሁበት ዓመት ቀድሞ አደርግ እንደነበረው ከዩኒቨርስቲው በቢዝነስ ግቢ በቅርብ ርቀት በሚገኘው ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን ማገልገል ጀመርሁ:: በግቢ ጉባኤ ከተማሪነት እሰከ አስተማሪነት ለመድረስም ጊዜ አልፈጀብኝም:: የሀይማኖት ትምህርት ከሌሎች ተማሪዎች ይልቅ የማስተማር ቀድሞም መሰረቱ ነበረኝ:: የመጀመርያ ዓመት ትምህርቴን በሰኬት አጠናቅቄ ለዕረፍት ወደ ጎንደር ተመለስሁ::

ቀድማ መምጣቴን ያወቀችው ማንአህሎሽ ጎንደር ከተማው ላይ ሆና በናፍቆት ተቀበለችኝ:: አባ ባህሪን እንኳን ሰላም ሳልል ወደ ማን አህሎሽ ነበር የሄድሁት:: አብረን እንዴት እንደምንኖር፤እንድናወራ አልያም ከመንደራችን ውጭ ለመጀመሪያ ጊዜ እንድንገናኝ ፈልጋ እና ፍቅሯን ልትገልጥልኝ አስባ ይሆናል ብዬ ነበር:: እሷ ግን ሌላ ሀሳብ ውስጥ ገብታ አገኘኋት::

ከባህር ዳር ተነስቼ አራት ሰዓት አካባቢ ጎንደር ደረስሁ:: መጀመርያ እንዳገኘኋት ወደ ጎንደር ከተማ የመጣችው እኔን ለመቀበል መስሎኝ ነበር:: አልጋ ከያዘችበት አብሬያት ካረፍሁ ከሰዓታት በኋላ አንድ ነገር እንድናደርግ ጠየቀችኝ::

ሙሉ ጤንነትህን ካልተመረመርህ ብላ አስጨነቀችኝ:: ለምን መመርመር እንዳስፈለገኝ ባላውቅም የእሷን ደስታ ለማየት ተስማማሁ:: ከባህር ዳር ከመጣሁ አንድ ቀን አላደርሁም አጣደፈችኝ:: በከተማው ብዙ ሆስፒታሎች ቢኖሩም እሷ ግን ወደ አንድ የእስራኤላውያን ሆስፒታል ነበር የወሰደችኝ:: ምርመራው ያለምንም ክፍያ በነፃ በመሆኑ በዛውም ጤንነቴን እንዳረጋግጥ እየጋበዘችኝ ነበር:: በዚያ ሆስፒታል እሷው እንዳለችኝ ሙሉ ጤናየን ለመመርመር ወሰንሁ:: ይሄም ሆነ...

ሆስፒታሉ ከገባሁ ከአንድ ሰዓት በኋላ የምርመራ ውጤቱ መጣና በውጤቱ ሙሉ ጤነኛ እንደሆንሁ ታወቀ:: ለማንአህሎሽም በዚህ የተነሳ ደስ እንዲላት ነገርኋት:: ይሄን ተከትሎ ግን አንድ ነገር መጣ... በምርመራው ሂደት የዘረመል ምርመራ መኖሩን ባላወቅሁበት ሁኔታ ዘሬ ከቤተ እስራኤላዊ የሌዊ ዘር የሚመዘዝ እንደሆነ ታወቀ: : ግራ ገባኝ:: እንዴት? ምናልባት በአባቴ? የተነሳ ነውስ በእናቴ? አልሁ ለራሴ... እራሴን ደጋግሜ ጠየቅሁት:: አባቴ ደግሞ ዘሩ የሚመዘዘው ከጎንደር ባላባቶች ነው:: የእናቴን፣ አባት እና አያቶቼን አላውቃቸውም:: ማንአህሎሽ ምናልባት ከተማው ላይ ብዙ ሆስፒታሎች እያሉ ወደዚህ ያመጣችኝ ይሄን ለማወቅ ይሆናል::

ብዙም አልቆየሁም የእነሱ ቤተሰብ በሙሉ ይሄን ቀድመው ማወቃቸውን ሰማሁ:: በዚህም ሙሉ ጤነኛ እንደሆኑ ዘራቸው እንደ እኔ የሌዊ ዘር መሆኑን አረጋግጥሁ:: ከማንአህሎሽ ጋር የሄድሁበት የእስራኤላውያን ሆስፒታል ሌላው ድብቁ ዓላማ ይሄ ነበር:: ከምርመራዬ በኋላ የዚሁ ሆስፒታል አንድ መሀመድ የሚባል ነጭ ሀኪም...

"ለኢትዮጵያ ቤተ-እስራኤላውያን እስራኤል ሁለተኛዋ ሀገራቸው ናት ስለዚህ ወደ ቅድመ አያቶችህ ሀገር ለመሄድ ዝግጅት መጀመር ትችላለህ::" ብሎ ነገረኝ:: ዛሬ ከእስራኤላውያን ወገን እንደሆንሁ አያቶቼም የካህኑ የሌዊ ዘር እንደሆኑ አውቄያለሁ:: እስራኤላውያን በትንሹ ከሊኒካቸው በእርዳታ፣ በትምህርት እያሳበቡ የራሳቸውን አጀንዳ እያስቀጠሉ ነበር:: በእርዳታ ስምና በበጎ ፍቃድ አሳበው ክሊኒኮች፣ ትምህርት ቤቶች እንዲሁም ሌሎች ነገሮች እየተከፈቱ ኢትዮ-እስራኤላውያን ጤነኛ የሆኑትን እና የተማሩ የሚፈልጓቸውን ብቻ በድብቅ ይወስዳሉ::

እነሱ እንደሚሉት የሌዊ ዘር ብሆንም ወደ እስራኤል መሄዱ ደንታ አልሰጠኝም:: ማንአህሎሽ ግን ቀድማ እንድመረመር ያደረገችኝ ውጤቴን እንድናውቅ ከዛ ቤተ-እስራኤላዊ ልሆን እንደምችል እንዲሁም እስራኤል ለመሄድ ዝግጅት እንድጀምር በአስደናቂ ነገር ልትነግረኝ አስባ ነበር::

ማን አህሎሽ ብዙ የኛ አካባቢ ሰዎች ይህን እንዳደረጉ፣ እሷና ቤተሰቦቿም ቤተ-እስራኤላዊ መሆናቸውን ማረጋገጣቸውን፣ ፈጣሪ ካለ ወደ እስራኤል ለመሄድ እንደሚችሉ ከወራት በፊት ዝግጅቱን እንደጀመሩ እኔም ይሄን ማድረግ እንደምችል አጫወተችኝ:: በሰው ዓይን ከኢትዮጵያ እስራኤል በሁሉም ነገር የላቀች ሀገር ነች:: ቢሆንም እኔ ከኢትዮጵያ መውጣትን አልሻም ነበር::

ማታ ሻይ እየጠጣን...

"ወሰድሽኝ ለዚህ ነበር ያው አንችን አንቢ ማለት ሰለከበደኝ ነው ወደ ሆስፒታል የሄድሁት... ማንአህሎሽ እኔ ከኢትዮጵያ መውጣት አልፈልግም::" መልሴን አጠር ባለ አማረኛ ነገርኋት...

"አንተ ደግሞ ኢትዮጵያ ውስጥ ምን አለ? እስራኤል የተሻለ ኑሮ ይኖረናል እኛም ለዚያ ነው የምንሄደው"

"አይ አልሄድም መሄድ አልፈልግም:: ለእናንተ ከተመቻችሁ እና ይሄን እኔ ካወቅሁ ምናልባት አስቤበት እመጣለሁ::" አልኋት

"ከእኔ፣ ከአባቴ እና እማዬ መለየት ትፈልጋለህ ማለት ነው?" ጠየቀችኝ::

"አልፈልግም ግን እናንተ የመረጣችሁት ለእናንተ ትክክል ነው:: የእኔም ምርጫ እንደዚያ አይደለም ከኢትዮጵያ መውጣት አልፈልግም::"

"እሺ ከዚህ እዚያ ይሻላል ተው ነገ ከነገ ወድያ ከዚህ ሀገር መውጫ አታገኝም!"

"አይ እኔ ከኢትዮጵያ ለመውጣት አልፈልግም አንች አብረሽኝ መሆን ከፈለግሽ ከዛ መቅረት አለብሽ..." አልኋት:: አሁን ለምን እንደሆን ከድሮው የተለየ ስሜት ነበራት:: እንደቀደመው አይደለችም ከእኔ ፍቅር አብሮነት ይልቅ ወደ እስራኤል መሄዱ ሳያጓጓት አልቀረም:: ምን ሰምታ እና አይታ እንደሆነ ግን አላውቅም::

"አንች እዚህ ኢትዮጵያ ብትቀሪ አይሻልሽም?"

"እሺ ተው ኢትዮጵያ አላደርገውም:: እንዳልሁህ ሀገሬ ነች አወዳታለሁ ግን ምንም ለውጥ የለባትም:: ለኑሮ አትመችም:: አደጋኋም ቁልቁል ነው:: ምነው እንደ ማያውቅ ሰው ሆንህ? ብዙ ሰዎች እኮ እስራኤል በመሄዳቸው ተለውጠው ዘመዶቻቸውንም አየለወጡ ነው::"



"ይሆናል እና አንች ለውጥ እንደምታመጪኝ በምን እርግጠኛ ሆንሽ?"

"እሱን አላውቅም ብለህ መናገርህ ነው:: በቅርብህ ብዙ ሰዎች እንደተለወጡ አንተም ታውቃለህ::" ማንአህሎሽ ለእኔ ያላት ፍቅር በእስራኤል ፍቅር እንደተሸረሸረ ተገንዝቤያለሁ:: ባለመመለሳችን ውስጥ ሁነን አመሸን:: በየግላችን ለራሳችን በምንጓዘው መንገድ ሁለታችንም ትክክል ነበርን::

መሸቶ ወደ አልጋ ክፍላችን ገባን:: በአንድ አልጋ ላይ አንሶላና ብርድ ልብስ ለብሰን በከንፈር ከመሳሳም ከመደባበስ ውጭ ሌላ ግንኙነት ሳይኖረን በደስታ በፍቅር እና በስሜት እሩቅ ተጓዝን:: ግብረ ስጋ ግንኙነት አልፈጸምንም ድንግልናዋን ከጋብቻ በፊት ልዝ አልፈለግሁም:: እሷ ደግሞ ወደ እስራኤል ልትሄድ ነው:: ጎዳና ወድቄ እንዳልቀር ህይወት ያስቀጠለችልኝን ልጅ ህይወቷን ላበላሸው አልፈለግሁም:: ምናልባት እሷ ምን ሀሳብ እንዳላት አላውቅም:: እኔ ግን አላደረግኩትም::

ነጋ ጠዚችንን አብረን ወደ መንደራችን አደረግን::

እስራኤላውያን ኢትዮጵያ ውስጥ ያለውን በትርክት የኛ ነው ያሉትን የሌዊ ዘር መሰረት በማድረግ በደብረ-ዘይት፣ ዝዋይ፣ሳንደር፣ ጎጃም፣ ደብረ ሊባኖስ አካባቢ፣አክሱም እና ሀዋሳ በትምህርት ቤት፣ በሆስፒታሎች በሚሸነሪ ሰበብ ሰዎችን ወደ ሆስፒታል እና ትምህርት ቤቶች በማስገባት የሚፈልጓቸውን ሰዎች በድብቅ ማጓዛቸውን ቀኒ እያልሁም ቢሆን አወቅሁ:: በግብረ-ሰናይ ድርጅቶች ስም የሚደረገው ህዝብን በስውር ከየሀገሮች መሰብሰብ በብዙ ሀገሮች እንዲሁም እዚህ ኢትዮጵያ ውስጥ መኖሩን አውቄያለሁ:: ኢትዮ-እስራኤላውያንን ከኢትዮጵያ የማውጣቱ ስራ እስከ መቼ እንደሚቀጥል ባላውቅም አሁንም ሲወስዱ እንደቀደመው ሙሉ በሙሉ ሁሉንም የሌዊ ዘሮችን ሳይሆን ወጣት፣ ይጠቅመናል ብለው

ሶሚየስበትን የተማረ እና ሙሉ ጤነኛ የሆነ ለስራ የተሰናዳ ሰው ሆኗል::

የአረፍት ጊዜዬን በቤት ሳሳልፍ የማንአህሎሽ አባት እና እናት ስብሀትም ጭምር ወደ እስራኤል አብሬያቸው እንድሄድ ደጋግመው እንዳይቆጨኝ አስጠንቅቀው አወሩኝ:: አልተቀበልኋቸውም... እኔ የእሷን ሀሳብ ሳልቀበል እሷም የኔን ሃሳብ ሳትቀበል የአንዳችን ሀሳብ አንዳችንን ሳይስብ አረፍቴ ተጠናቀቀ:: አብረን በፍቅር ብናሳልፍም ነገሮች በአንድ ዓመት ተለውጠው ጠብቀውኝ ነበር:: ወደ ዩኒቨርስቲ የምሄድበት ቀን ደረሰ:: ፈጣሪ ብሎ ካልሄዱ ዳግም የሁለተኛው ዓመት ትምህርት ሲያበቃ እንደምንገናኝ ተነጋግረን እየተነፋፈቅን ከማንአህሎሽ እና ከቤተሰበቧ ጋር ተለያየን:: ጉዞዬን ወደ ጅማ ዩኒቨርስቲ አደረግሁ::

***

የአንደኛው ሴሚስተር የመጨረሻ ፈተና ዝግጅት ላይ በነበርሁ ሰዓት ነበር ማንአህሎሽ ደውላ ወደ እስራኤል ለመሄድ ሁሉን ዝግጅት ጨርሰው ለጉዞ አንድ ወር እንደተስጣቸው የነገረችኝ:: መውጫ ጊዜያቸው እንደዚህ መፍጠን አስገረሞኛል::

ማንአህሎሽ ስልክ ደውላ

"መጥተህ አትሸኘንም?" አለችኝ

"እንዴ ፈተና ስጨርስ በዓመቱ መጨረሻ እመጣለሁ:: ፈተና ደርሷል..." አልኋት ያኮረፈች መሰለኝ::

"እንደዚህ እሩቅ ለሩቅ ሁነን ነው በቃ የምትሸኘኝ?"

"ስትሄዱ ንገሩኝ እሸ?" ጠየቅኋት

"ምን ታደርጋለህ ለምትወደው ሰው?"

"ምን ማለት ነው?" እኔም ውስጤ እየተጨነቀ ነበር::

"እሸ አትሸኘኝም ማለት ነው?"

"እንዴት አድርጌ ማንአህሎሽ? አልችልም ፈተና ላይ ነኝ ልትወጡ ስትሉ እመጣለሁ::"

"አንተ አትወደኝም አትወደኝም" አልቅሳ ሰልኩን ጆሮዬ ላይ ዘጋችው:: ዳግም ሀሳቧን ለመስማት ሰል ደውዬ ነበር:: ሰልኳ አይሰራም ከዛን ቀን ጀምሮ የተዘጋ ስልኳን እሷንም ዳግም ላገኛት አልቻልሁም:: ከልጅነት እስከ እውቀት ያሳለፍነውን ትዝታዋን በልቤ ይዤ ስትርቀኝ ተሰማኝ:: ያም እውነት ሆነ... ቀናት ሲሄዱ አባቷን፣ እናቷን፣ወንድሟን እና እሷን ላላይ የጉዟችን ቀን አባቷ ደውሎ የወላጅ አባቴን ቤቱን መሬቱን ሁሉን እንደሸጠ በመንገር ብዙ ሺህ ብር በባንክ አስገብቶልኝ ለመሄድ አዲስ አበባ መሆናቸውን ነገረኝ:: ልሸኛቸው ፈለግሁ:: በዛው ቀን ነበር የሚሄዱት:: ትንሽ ስለቸልተኝነቴ እና እነሱን ሳልሸኝ በመቅረቴ ተናደድሁ:: ቀድሜ ቼልተኛ ባልሆንና ብሄድ አገኛቸው ነበር:: ሲሄዱ ቅር ብሰኝም ከጅማ ዩኒቨርስቲ ሳልወጣ ተሰነባበትን:: ራሴን ታዘብሁት ከሄዱ በኋላ ሆነ የግድ ብዬ መሸኜት እንደነበረብኝ ውስጤ ደጋግሞ እየነገረ ወቀሰኝ::